# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን

## የኢንዱስትሪ ፓርኮች የተቀናጀ የደረቅ እና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ውጤታማነትን በተመለከተ የተከናወነ የአካባቢ ኦዲት ሪፖርት







መጋቢት/ 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ

**ማውጫ** ........ **I**

**የቃላት ትርጓሜ** ........ **I**

**የአካባቢ ኦዲቱ ማጠቃለያ** ........ **1**

**ክፍል አንድ** ........ **4**

መግቢያ ........ 4

የኮርፖሬሽኑ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዓላማ እና ሥልጣን ........ 5

**ራዕይ** ........ **5**

የቦርዱ (የኢንቨስትመንት ቦርድ) ዋና ዋና ተግባራት ........ 5

የኮርፖሬሽኑ ሥልጣንና ተግባር ........ 5

የአካባቢና ማህበራዊ ጉዳዮች መምሪያ ዋና ዋና ተግባራት ........ 6

የኢንዱስትሪ ፓርኮች የደረቅ እና የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ የአሰራር ሥርዓት ........ 3

የኮርፖሬሽኑ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል ........ 4

*የኮርፖሬሽኑ ድርጅታዊ መዋቅር* ........ *4*

*የኮርፖሬሽኑ የሰው ሃይል* ........ *4*

የኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ ምንጭ ........ 4

የአካባቢ ኦዲቱ ዓላማ ........ 5

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ........ 6

*የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች* ........ *6*

የአካባቢ ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ........ 7

*የአካባቢ ኦዲቱ ወሰን* ........ *7*

*የአካባቢ ኦዲቱ ዘዴ* ........ *7*

**ክፍል ሁለት** ........ **8**

**ዋና ዋና ግኝቶች** ........ **8**

*የኢንዱስትሪ ፓርኮች ሲገነቡ የአካባቢና የማሕበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ ሪፖርት ቀርቦ ተገምግሞ ፈቃድ የተሰጣቸው ስለመሆኑ በተመለከተ፤* ........ *8*

*በኢንዱስትሪ ፓርኮች የዝቃጭ አያያዝና አወጋገድ ስርአትን በተመለከተ፡* ........ *10*

*የአረንጓዴና የጋራ ቦታዎች እንክብካቤ ልማት ተግባራዊነት እና ከፓርኮቹ የሚመነጩ ቆሻሻዎች አያያዝ ስልቶች ክትትል መደረጉን በተመለከተ* ........ *13*

*ከፍሳሽ ማከሚያዎች የሚመነጨን ዝቃጭ ቆሻሻ ለማስወገድ በዕቅድ ተይዞ የሚተገበር እና የሳኒተሪ ላንድ ፊል መዘጋጀቱን በተመለከተ* ...... 17

*በኢንዱስትሪ ፓርኮች ቆሻሻን ለማስተዳደር የሚያስችል ስርአት ተዘርግቶ ክትትል መደረጉን በተመለከተ* ...... 19

*የአካባቢ ደህንነትንና ጥበቃን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር የሚሰሩ መሆናቸውን በተመለከተ፤* ...... 24

*ኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚጠቀሟቸው ኬሚካሎች አቅርቦት እና መረጃ አያያዝና ሪፖርት በተመለከተ* ...... 27

*በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ለሚሰሩ ሰራተኞች ስለ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ የግንዛቤ ማስጨበጫ መሰጠቱን በተመለከተ፡* ...... 29

*የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ ግንባታ በዲዛይኑ መሰረት በወቅቱ ተጠናቀው ወደ ስራ መግባታቸውን በተመለከተ፡* ...... 30

*የለማ ኢንዱስትሪ ፓርክን ለአምራች ድርጅቶች ያቀረበ/ያስተላለፈ መሆኑን በተመለከተ* ...... 31

*ለ72 ሰአታት የፍሳሽ ቆሻሻ የሚይዝ የፍሳሽ ማጠራቀሚያ ታንከር መገንባቱን በተመለከተ* ...... 32

*አምራች ድርጅት በጊዜያዊ የማከማቻ ስፍራ አደገኛ ቆሻሻን ከአንድ ወር በላይ የማያከማች መሆኑን በተመለከተ፡* ...... 32

*ኮርፖሬሽኑ ለአምራች ድርጅቶች የፍሳሽ መለኪያ መሳሪያ እንዲገጠም ማስደረጉን በተመለከተ* ...... 35

*በኢንዱስትሪ ፓርኮች አምራች ድርጅቶች የሚለቁትን ፍሳሽ መጠንና ይዘትን መሰረት ያደረገ ክፍያ ስርዓት በተመለከተ* ...... 36

*አምራቾች ከሚለቁት ፍሳሽ የሚሰበሰብ ገቢ ተመጣጣኝና ወቅታዊ ማስተካከያ የሚደረግበት መሆኑን በተመለከተ፡* ...... 37

**ክፍል ሶስት ...... 39**

**መደምደሚያ ...... 39**

**ክፍል አራት ...... 42**

**የማሻሻያ ሃሳቦች ...... 42**

**አባሪ 1፡የአካባቢና ማህበራዊ ጉዳዮች መምሪያ ዝርዝር ተግባራት** ...... 44

**አባሪ 2፡ የኢ/ፓ የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ የአሰራር ስርዓት ...... 46**

**አባሪ 3፡ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ኮርፖሬሽን ድርጅታዊ መዋቅር ...... 48**

**አባሪ 4፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች(EVALUATIVE CRITERIA) ...... 49**

**አባሪ 5፡ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው መጠይቅ የቀረበላቸው እና የመስክ ጉብኝት የተደረገባቸው ኢንዱስትሪ ፓርኮችና የሚመለከታቸው አካላት ዝርዝር ...... 54**

**አባሪ 6፡ በኦዲቱ ወቅት የተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች ዝርዝር፡- ...... 55**

# የቃላት ትርጓሜ

**“ኢንዱስትሪ ፓርክ“** ማለት የኢንዱስትሪ እድገትን ፣ብክለት በአካባቢና በሰው ላይ የሚያደርሰውን ተፅዕኖ መቀነስንና የከተሞች ዕድገት በዕቅድና በስርአት መምራት ዓበይት ዓላማዎችን የያዘ ሆኖ ዕቅድን መሰረት አድርጎ እንደ መንገድ፣ የኤሌክትሪክ ሓይል ፣ ውሃ፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎት እና የመሳሰሉ አስፈላጊ መሰረተ ልማቶች ተሟልተውለት እና ልዩ የማበረታቻ ዕቅድ ኖሮት ፣ ሁሉን አቀፍ ፣ የተቀናጀ ፣ ፊርጀ-ብዙ ወይም አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይነት ያላቸው ኢንዱስትሪዎች በተመጋጋቢነት ለማልማት የሚቋቋም ፣ ድንበር የተበጀለት በቦርድ የተሰየመ የተወሰነ ቦታ ሲሆን ልዩ የኢኮኖሚ ቀጠና ፣ የቴክኖሎጂ ፓርክን ፣ የኤክስፖርት ማቀነባበሪያ ቀጠናን ፣ የአግሮ-ፕሮሰሲንግ ቀጠናን ፣ ነፃ የንግድ ቀጠናን እና ሌሎች ተመሳሳይ በኢንቨስትመንት ቦርድ የሚሰየሙትን ይጨምራል፡፡

**“የለማ መሬት“** ማለት እንደ መንገድ ፣ ውሃ ፣መብራት ፣ ስልክ ፣ ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ስርአት ፣ የአየር ብክለት መቀነሻ ስርአት እና የመሳሰሉት አስፈላጊ መሰረተ ልማቶች የተሟሉለት መሬት ነው፡፡

**“የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ“** ማለት አንድ ፕሮጀክት ወይም መንግስታዊ ሰነድ ተግባራዊ ሲሆን የሚያስከትለውን ገንቢም ሆነ አፍራሽ ውጤት በቅድሚያ ለይቶ የማወቂያና የመመዘኛ ዘዴ ነው፡፡

**“ተፅዕኖ“** ማለት በአካባቢ ወይም በንዑሳን ክፍሎቹ ላይ በሚፈጠር ለውጥ ምክንያት ማንኛውም በሰው ጤና ወይም ደህንነት፤ በዕፅዋት፤ በእንስሳት፤ በአፈር፤ በአየር፤ በውሃ፤ በአየር ንብረት፤ በተፈጥሮአዊ ወይም በባህላዊ ቅርስ፤በሌላ ቁሳዊ ቁም አካል፤ወይም በአጠቃላዩ ሲታይ በአካባቢያዊ፤ በማህበራዊ፤ በኢኮኖሚያዊ ወይም በባህላዊ ገፅታዎች ላይ የሚከሰት ተከታይ ለውጥ ነው፡፡

**“የኢንዱስትሪ ኬሚካል“** ማለት ለኢንዱስትሪ፤ ለትምህርት፤ ለስልጠና፤ ለምርምርና ስርፀት አገልግሎት ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውም ኬሚካል የሚጨምር ሲሆን የመድሃኒትና የህክምና ፤የምግብና የምግብ ነክ፤ የግብርና፤ የኬሚካል ጦር መሳሪያዎች እና የጨረር አመንጪ ኬሚካሎችን አይጨምርም

## የአካባቢ ኦዲቱ ማጠቃለያ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት በኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ በአገር ደረጃ የተያዙትን የልማት ግቦች እውን በማድረግ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግርን ለማረጋገጥ እና የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉን ቀዳሚ የልማት አጀንዳ አድርጎ ለመንቀሳቀስ በርካታ ስራዎች በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ከከተሞች እድገት ጋር ተያይዞ አገራዊ ስፓሻል ማስተር ፕላንን የተከተለ እንዲሆን እና የኢኮ-ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት የመንግስት ስትራቴጂ አካል በመሆን ተግባራዊ በመደረግ ላይ ነው፡፡

በመሆኑም የኢንዱስትሪ ፓርክ ልማት ዋና ዓላማው ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን በአንድ ቦታ በማሰባሰብ የሃብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ከማረጋገጥ ባለፈ ከኢንዱስትሪዎች በጠጣር፤ በፈሳሽ ወይም በጋዝ መልክ በመለቀቅ በአካባቢና በማህበረሰብ ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ ችግሮችን በመቆጣጠር፤ብክለትን በመከላከል እና የኢንዱስትሪ ፍሳሽን በማከም ወይም በማጣራት ጥቅም ላይ እንዲውል ማስቻል ነው፡፡ ይህንኑ ዓላማ ምን ያህል እያሳካ እንደሆነ ለማወቅ መ/ቤታችን በኢንዱስትሪ ፓርኮች ኮርፖሬሽን "የኢንዱስትሪ ፓርኮች የተቀናጀ የደረቅ እና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ" በሚል ርዕስ የአካባቢ ክዋኔ ኦዲት አከናውኗል፡፡

የአካባቢ ኦዲቱ ዓላማ በኮርፖሬሽኑ የኢንዱስትሪ ፓርኮች የደረቅ እና የፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና የአካባቢ ጥበቃ መርሆዎችንና ህጎችን በተከተለ መልኩ ማከናወኑን በማረጋገጥ በሥራው ዙሪያ የሚታዩ የአሠራር ችግሮች ወይም ክፍተቶች ካሉ በመለየት ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

የኦዲቱን ዓላማ ለማሳካት በተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Audit Area) ስር አራት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) የተለዩ ሲሆን፤ እነሱም፡-

- ኮርፖሬሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ያሉት ኢንዱስትሪዎች የሚያመነጩት ደረቅ እና ፈሳሽ ቆሻሻ በተገቢው መንገድ ለመሰብሰብ ለማስወገድ እና መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያግዙ የማስፈፀሚያ መመሪያዎች፣ ማኑዋሎች እና ደረጃዎች መዘጋጀታቸውን እንዲሁም የአሰራር ስርአት መዘርጋቱንና ተግባራዊ ስለመደረጉ ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን ማጣራት፤
- ኮርፖሬሽኑ ኢንዱስትሪ ፓርኮችን ሲገነባ የደረቅና የፍሳሽ ማስወገጃ ሁኔታዎችን ባገናዘበ መልኩ ዲዛይን ማድረጉንና ቦታዎችን ማዘጋጀቱን ማጣራት ፤
- ኮርፖሬሽኑ የኢንዱስትሪ ፓርኮች የስራ ቦታና ግቢ በሰራተኞች ደህንነትና ጤንነት ላይ አደጋ የማያስከትል መሆኑን መገምገም፤

- ኮርፖሬሽኑ የአካባቢ ደህንነትን በጠበቀ መልኩ ስራውን እንዲሰራ ከሚያግዙት ባለ ድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበት የአሰራር ስርአት የዘረጋ እና የተደራጀ የመረጃ አያያዝ መኖሩን መገምገም ፣

  የሚሉት ናቸው፡

ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ሲሆን በኢትዮጵያ የክዋኔ የኦዲት ስታንዳርድ እንዲሁም ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሰረት በናሙና በተመረጡ ኢንዱስትሪ ፓርኮቹ ለሚመለከታቸው የስራ ሀላፊዎችና በከተማው የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በአካል በመገኘት ቃለ መጠይቅ በማቅረብና ተጠይቀው የቀረቡ ተያያዥነት ያላቸውን ማስረጃዎችን በመሰብሰብና በመከለስ ነው፡፡

በኦዲቱ ወቅት የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች፡-

- ኢንዱስትሪ ፓርኮች ሲቋቋሙ የተጠናላቸው የአካባቢያዊ እና የማህበራዊ ተጽዕና ግምገማ (ESIA-Environment and Social Impact Assessment) ጥናት አንድ ማዕከላዊ ጥናት ማለትም ለቴክስታይልና ጋርመንት ዘርፍ ብቻ ሲሆን፤ጥናቱ የማያካትታቸው ዘርፎች- የቀለም ፋብሪካ፤ ማዳበሪያ (የሲሚንቶ ከረጢት) ማምረቻ፤ ፕላስቲክ (ለታሸገ ውሃ ግብአት) የሚሆን ማምረቻ፤ የኮቪድ 19 ቴስት ኪት ማምረቻ የመሳሰሉት ድርጅቶች የአካባቢያዊ እና የማህበራዊ ተጽዕና ግምገማ ጥናት ሳይጠናላቸው በኢንዱስትሪ ፓርኮቹ የማረት ስራ ጀምረው እየሰሩ ያሉ መሆኑ፤
- በኢንዱስትሪ ፓርኮች ከፍሳሽ ማጣሪያ የሚገኝ ዝቃጭ (በተለይ በሐዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ) ለረጅም ጊዜ በፓርኩ ግቢ ውስጥ ለዝናብ በተጋለጠ ሁኔታ ከ5 ዓመታት በላይ ተከማችቶ የሚገኝና በዝናብ ወቅትም እየታጠበ ከዝናብ ፍሳሽ ጋር እንደሚወርድና የግቢውን ውበት እያበላሸ መሆኑ፤
- በአዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ እና በቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ ስር የሚገኙት ፋብሪካዎች ፍሳሻቸውን ወደ አካባቢው ማህበረሰብ የሚለቁ መሆናቸው እና በተለይ በቦሌ ለሚ የሚገኘው ፋብሪካ ፍሳሹ ወደ ማሳ (እርሻ) የሚገባ እና ከማጣሪያውም መጥፎ ሽታ የሚወጣ መሆኑ ፤
- በአዋጅ ቁጥር 886/2007 አንቀጽ 24 መሰረት የአካባቢ ስርዓቶችን፤ ደረጃዎችን፤ የአካባቢ መንከባከቢያ መንገዶችን እና የአካባቢ ጉዳት መቀነሻ ዕቅዶችን በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ለማስፈጸም፤ ለመቆጣጠር፤ ለመጠበቅ እና ተግባራዊ ለማድረግ የሚያግዝ ቢሮ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ እንደሚደራጁ ቢገልጽም ኮርፖሬሽኑና የኢ.ፌ.ድ.ሪ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በመተባበር ቢሮው ያልተቋቋመ መሆኑ፤

- ደብረ ብርሃን እና ባህር ዳር ኢንዱስትሪ ፓርኮች የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ ግንባታ ስራዎች በኮርፖሬሽኑ አመታዊ ዕቅድ ማለትም በ2013 ዓ.ም እና በ2014 ዓ.ም 100% ለማጠናቀቅ ዕቅድ የተያዘ ቢሆንም፤ በተያዘው መሰረት ዕቅድና በወቅቱ ተጠናቀው ወደ ስራ ያልገቡ መሆኑ፤

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ከላይ ለተመለከቱት ዋና ዋና ግኝቶች መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ኮርፖሬሽኑ የአካባቢያዊ እና የማህበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ ካስጠናባቸው ዘርፎች-ከቴክስታይልና ጋርመንት ውጪ ያሉ የስራ ዘርፎችን ይዘው ወደ ፓርኮች ለሚገቡ ባለሃብቶች የአካባቢ እና የማህበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት እና የአካባቢ አስተዳደር ዕቅድ አዘጋጅተው እንዲገቡ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ከፍሳሽ ማጣሪያ የሚገኝ ዝቃጭ በተለይም በዝናብ ወቅት እየታጠበ ከዝናብ ፍሳሽ ጋር እየወረደ የውሃ አካላትን እንዳይበክል፤ በአግባቡ የሚይዝበት፤የሚያስወግድበት ወይም በጥናት ለሌሎች ምርት እንደ ግብአት የሚያገለግልበትን አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ ሁሉም አምራች ፋብሪካዎች ፍሳሻቸውን ወደ አካባቢው እንዳይለቁ ሊያደርግና ከፍሳሽ ማጣሪያቸው የሚወጣው መጥፎ ሽታ እንዲወገድ (እንዲቀንስ) ማድረግ የሚቻልበትን መንገድ ከባለሃብቶቹ ጋር በመነጋገር መፍትሄ እንዲያገኝ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ በአዋጅ ቁጥር 886/2007 አንቀጽ 24 መሰረት የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር ላይ ከሚሰሩ ልዩ ልዩ ተቋማት ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር የአካባቢ ጉዳት መቀነሻ ዕቅዶችን በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያግዝ የአከባቢ ጥበቃ ቢሮ በባለሙያ እንዲደራጅ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ የደብረ ብርሃን እና ባህር ዳር ኢንዱስትሪ ፓርኮች የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ የግንባታ ስራዎች መጓተትን መፍትሄ በመስጠት እንዲጠናቀቁና አላስፈላጊ ወጪዎች እንዳይከሰቱ ሊያደርግ ይገባል፤

የሚሉት ይገኙበታል፡፡

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት በኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ በአገር ደረጃ የተያዙትን የልማት ግቦች እውን በማድረግ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግርን ለማረጋገጥ እና የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉን ቀዳሚ የልማት አጀንዳ አድርጎ ለመንቀሳቀስ በርካታ ስራዎች በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ከከተሞች እድገት ጋር ተያይዞ አገራዊ ስፓሻል ማስተር ፕላንን የተከተለ እንዲሆን እና የኢኮ-ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት የመንግስት ስትራቴጂ አካል በመሆን ተግባራዊ በመደረግ ላይ ነው፡፡
2. በመሆኑም ይህንኑ የልማት ግቦች እውን ለማድረግ የኢንዱስትሪ ፓርክ ልማቱን በበላይነት የሚመራ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 326/2007 ከመንግስት በሚያገኘው ሁለንተናዊ ድጋፍ በ2007 ዓ.ም የተቋቋመ የመንግስት የልማት ድርጅት ነው፡፡
3. ከጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት ግንቦት 27/2010 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር መ150-851/1 እንደተጠቀሰው ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፓርኮች ኮርፖሬሽን ከነሙሉ መብትና ግዴታው ለኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን እንዲያስረክብ በመወሰኑ በኢ.ፌ.ድ.ሪ የፌደራል አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1097/2018 እንደተወሰነው የኢንዱስትሪ ፕሮጀክት አገልግሎት ከነሙሉ መብትና ግዴታው ለኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን አስረክቧል፡፡ ባደጉትና በማደግ ላይ ያሉ የተለያዩ ሀገራት ልምድ እንደሚያሳየው የኢንዱስትሪ ፓርኮች ሰፊ የስራ እድልን በመፍጠር፣ የኤክስፖርት ገቢን በማስገኘት፣ የኢኮኖሚ እድገትን በማስመዝገብ፣ ቴክኖሎጂን በማስተዋወቅና በማስፋፋት እንዲሁም ከተማዎች እንዲስፋፉ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ በሀገራችንም ይህንን ዕድል ለመጠቀም የኢንዱስትሪ ፓርኮችን በማልማት ወደስራ በመግባት ላይ ናቸው፡፡
4. የኢንዱስትሪ ፓርክ ልማት አንዱ እና ዋናው ዓላማ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን በአንድ ቦታ በማሰባሰብ የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ከማረጋገጥ ባለፈ ከኢንዱስትሪዎች በጠጣር፣ በፈሳሽ ወይም በጋዝ መልክ በመልቀቅ በአካባቢና በማህበረሰብ ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ ችግሮችን በመቆጣጠር እና ከነዚህም ውስጥ የኢንዱስትሪ ፍሳሽን በማከም እና በማጣራት ጥቅም ላይ እንዲውል በማስቻል እንዲሁም ብክለትን ከማስቀረት ባሻገር የተፈጥሮ ሃብትን ለመቆጠብ ትልቅ ፋይዳ የሚኖረው ተግባር በመሆኑ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን የደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ በትኩረት ሊሰራ የሚገባው ተግባር ነው፡፡

## የኮርፖሬሽኑ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ሥልጣንና ተግባር

### ራዕይ

5. በ2017 የዓለም ምርጥ ኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚና አስተዳዳሪ መሆን፡፡

**ተልዕኮ**

- ኢንዱስትሪ ፓርኮችን በማልማትና በማስተዳደር ለዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር፣የወጪ ንግድን ማሳደግ እና ኢንዱስትሪን በማስፋፋት ኢትዮጲያን የመካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለማሰለፍ ለሚደረገው ኢኮኖሚያዊ ልማት አስተዋፅኦ ማድረግ፤
- በኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ፈጠራንና ትግበራን በማስቀደም በእውቀት ላይ የተመሰረተ ህብረተሰብና ኢኮኖሚ ግንባታን ማፋጠን፤
- ለደንበኞቻችን ወቅታዊና ጥራት ያለው ዓለም አቀፍ ስታንዳርድ ያሟላ የምክርና የስልጠና አገልግሎቶችን በማቅረብ እርካታቸውን መጨመር፡፡

## የቦርዱ (የኢንቨስትመንት ቦርድ) ዋና ዋና ተግባራት

6. ቦርዱ (የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ) በሚኒስትሮች ም/ቤት በደንብ ቁጥር 417/2009 መሰረት የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት፣ ይኖሩታል፡፡

- የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት፣ አስተዳደርና አመራር፣ ተቋማዊ ግንባታና ቁጥጥርን በበላይነት የመምራት፤
- የአንድ ማዕከል አገልግሎትን በተመለከተ በሚመለከታቸው መንግስታዊ ተቋማት የትብብርና የቅንጅት ዘላቂ ስርአት መዘርጋቱን የማረጋገጥ፣

## የኮርፖሬሽኑ ሥልጣንና ተግባር

7. ኮርፖሬሽኑ በሚኒስትሮች ም/ቤት በደንብ ቁጥር 326/2007 መሰረት የሚከተሉት ዓላማዎች ተሰጥተውታል፡፡

- ✓ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን የማልማት፣ የማስተዳደር፣ የለማ ቦታ በሊዝ ማከራየት እና ግንባታዎችን የማከራየት ወይም በሽያጭ የማስተላለፍ፤
- ✓ የአገራዊ ስፓሻል ማስተር ፕላንን መሰረት በማድረግ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ዝርዝር ማስተር ፕላን የማዘጋጀት እና ከክልል መንግስታት ጋር በሚደረግ ስምምነት መሰረት መሬት በመረከብ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት መሬት ባንክ ሆኖ የማገልገል፤

- ✓ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አስፈላጊ መሰረተ ልማቶች ለኢንዱስትሪ ፓርኮች አልሚዎች ተደራሽ እንዲሆኑ የማድረግ፤
- ✓ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የኢንዱስትሪ ፓርኮችን የማስተዳደር ተግባር በስራ አመራር ውል ለሌሎች አካላት የማስተላለፍ፤
- ✓ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ጠቀሜታ በሰፊው በማስተዋወቅ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚሰማሩ ባለሀብቶችን የመሳብ ፤
- ✓ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሚያወጣውን መመሪያ እና የፖሊሲ አቅጣጫ መሰረት በማድረግ ቦንድ የመሸጥና በዋስትና የማስያዝ እና ከአገር ውስጥና ከውጭ የገንዘብ ምንጮች ጋር የብድር ውል የመደራደርና የመፈራረም፤
- ✓ አላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማች የሆኑ ስራዎችን ማካሄድ፡፡

የሚሉ ናቸው፡፡

## የአካባቢና ማህበራዊ ጉዳዮች መምሪያ ዋና ዋና ተግባራት

8. ለመምሪያው የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት ተሰጥቶታል

- ➢ የመምሪያውን ስራ ማቀድ፤ የታቀዱ ተግባራት በዕቅዱ መሰረት እንዲፈፀሙ መምራትና ማስተባበር፡፥
- ➢ የአካባቢና ማህበራዊ የተፅዕኖ ግምገማ እና የመልሶ ማስፈር ዕቅድ የጥናት ሰነዶች የይሁንታ ፈቃድ እንዲያገኙ እንዲሁም ይሁንታ በተገኘባቸው የጥና ሰነዶች መሰረት የአካባቢና የማህበራዊ አያያዝ ዕቅዶች እንዲፈፀሙ ይከታተላል፡፡ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚገነቡ የፍሳሽ ማጣሪያዎች የሀገር ውስጥ እና አለምአቀፍ የህግ ተከባሪነትን አሟልተው እንዲሰሩ የሙያ ድጋፍ ያደርጋል፡፡ የፓርኮች የመጠጥ ውሃ የጥራት ደረጃ እንዲረጋገጥ በመጠጥ ውሃ ማጣሪያ ግንባታ እና ኦፕሬሽን ወቅት ይከታተላል፤ የሙያ ድጋፍ ያደርጋል፡፡
- ➢ ሁሉም የኢንዱስትሪ ፓርኮች በሂደት Eko-Industry መርሆዎችን ያሟሉ እንዲሆኑ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ተቀራርቦ ይሰራል፡፡ የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት በተቀናጀ መልኩ ተግባራዊ እንዲደረግ የማስተባበር ስራ ይሰራል፡፡ የአረንጓዴ ልማት ስራ ደረጃውን በጠበቀ መንገድ እንዲከናወን እና ተገቢ እንክብካቤ እንዲደረግና ክትትል እና ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ ናቸው፡፡ ዝርዝር ተግባራቱ (በአባሪ 1 ተያይዟል)

## የኢንዱስትሪ ፓርኮች የደረቅ እና የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ የአሰራር ሥርዓት

9. በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ለባለሃብቶች ከሚሰጡ አገልግሎቶች መካከል አንዱ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገድ ሲሆን ከባለሀብቶች የማምረቻ ቦታዎች (ሸዶች) የሚመነጭ ደረቅ ቆሻሻ የሚወገደው ደረቅ ቆሻሻን በሚያነሱ ማህበራት አማካይነት ነው (ዝርዝር ተግባራቱ በአባሪ 2 ተያይዟል)

## የኮርፖሬሽኑ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል

### የኮርፖሬሽኑ ድርጅታዊ መዋቅር

10. ኮርፖሬሽኑ ተጠሪነቱ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በኩል ሆኖ ለጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት ሲሆን በቦርድ ይመራል፡፡ ኮርፖሬሽኑ በሚኒስትሮች ም/ቤት በደንብ ቁጥር 326/2007 መሰረት የተሰጠውን ስልጣን፣ ኃላፊነት ለመወጣት እንዲችል በዋና ስራ አስፈፃሚው ጽ/ቤት ስር 9 ዳይሬክቶሬቶች እና 3 ም/ዋና ስራ አስፈፃሚዎች ያሉ ሲሆን በስራቸውም 11 መምሪያዎች ያሉት ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ከኦዲቱ ጋር በቀጥታ የሚገናኘው በም/ዋ/ስ/አስፈፃሚ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ኦፕሬሽን ሲሆን በስሩ አራት መምሪያዎች ሲገኙ እነሱም፡- የኢንዱስትሪ ፓርኮች ድጋፍና ክትትል መምሪያ፤የአካባቢና ማህበራዊ ጉዳዮች መምሪያ፤ የፓርኮች ደህንነት መምሪያ እና ኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚባሉት ይገኛሉ፡፡(ድርጅታዊ መዋቅሩ በአባሪ 3 ተያይዟል)

### የኮርፖሬሽኑ የሰው ሃይል

11. ኮርፖሬሽኑ እስከ ሚያዝያ ወር 2014 ዓ.ም 239 (25.75%) ሴት ሰራተኞች 689 (74.24%) ወንድ ሰራተኞች፣ በድምሩ 928 ሰራተኞች ያሉት ሲሆን፣ **ኮርፖሬሽኑ** ያለው የሰው ኃይል በሙያ ሲተነተን ማስተርስ (ሴት) 25 ወንድ 103፣ የመጀመሪያ ዲግሪ ሴት 125 ወንድ 305፣ ዲፕሎማ ሴት 35 ወንድ 63 እና ሰርተፍኬት እና ከዛ በታች ያሉ ሴት 54 ወንድ 218 የነበሩት ሲሆን **ኮርፖሬሽኑ** እስከ መስከረም ወር 2015 ዓ.ም ድረስ 901 ቋሚ ሰራተኞች ሲኖሩት ወንድ 686 ሴት 215 ሲሆኑ ኮንትራት ሰራተኞች ደግሞ 134 ሰራተኞች (ወንድ 101 ሴት 33) ሲሆኑ በድምሩ 1036 ማለትም 787 (76%) ወንድ 248 (24%) ሴት ሰራተኞች ናቸው፡፡

## የኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ ምንጭ

12.ኮርፖሬሽኑ በሚኒስትሮች ም/ቤት በደንብ ቁጥር 326/2007 መሰረት የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለማስፈፀም ይረዳው ዘንድ ከመንግስት መደበኛ በጀት የሚመደብለት ሲሆን ከ2012-2014 በጀት ዓመት ድረስ የተመደበለት በጀት በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡ የበጀት አይነት ስር የተመለከቱት ሼባ፡-መንግስት ከቦንድ ሽያጭ ለኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት የተበጀተ በጀት-አይ.ዲ.ፒ፡- የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ (Industry Development Fund)፤ሼባ እና ትሬዥሪ በገንዘብ ሚኒስቴር የተያዙ ካፒታል በጀት እና አይ.ዲ.ፒ በወርልድ ባንክ የተያዘ ካፒታል ሲሆን ለቂሊንጦና ለቦሌ ለሚ ምዕራፍ(ፌዝ) ሁለት የተያዘ ነው፡፡

| የበጀት ዓመት | የበጀት ዓይነት | የተመደበ የፋይናንስ ድጋፍ (ብር) | በሥራ ላይ የዋለ (ብር) | ሥራ ላይ ያልዋለ (ብር) | አፈፃፀም በመቶኛ(%) |
|---|---|---|---|---|---|
| 2012 | ሼባ | 2,403,800,000.00 | 1,638,921,441.09 | 764,878,558.91 | 68 |
| | ትሬዥሪ | 608,111,128.05 | - | 608,111,128.05 | - |
| | አይ.ዲ ኤፍ | 209,680,000.00 | 84,528,964.90 | 125,151,035.10 | 40 |
| 2013 | ሼባ | 699,989,802.75 | 646,926,689.22 | 53,063,113.53 | 92.4 |
| | ትሬዥሪ | 1,182,282,750.05 | 675,151,519.07 | 507,131,230.98 | 57 |
| | አይ.ዲ ኤፍ | 190,890,000.00 | 11,853,494.25 | 179,036,505.75 | 6 |
| 2014 | ሼባ | - | 142,398,691.08 | 142,398,691.08 | * |
| | ትሬዥሪ | 1,838,994,721.00 | 1,152,187,623.37 | 686,807,097.63 | 63 |
| | አይ.ዲ ኤፍ | - | 40,602,193.69 | 40,602,193.69 | * |
| 2015 | ትሬዥሪ | 2,413,472,310.00 | የለም | 2,413,472,310.00 | ** |

መግለጫ ፡- የ2014 ዓ.ም በጀት የሚያሳየው እስከ ሚያዝያ ወር ያለውን ነው፡፡

* የተመደበ በጀት ባይኖርም የክፍያ ጥያቄ እየተላከ ሲፈቀድ የተከፈለ ነው፡፡

**በ2015 በጀት ዓመት በጀት የፀደቀው ዘግይቶ የነበረ በመሆኑ በሶስት ወሩ ውስጥ ምንም ክፍያ አልተፈፀመም፡፡

## የአካባቢ ኦዲቱ ዓላማ

13. የአካባቢ ክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ ኮርፖሬሽኑ የኢንዱስትሪ ፓርኮች የደረቅ እና የፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና የአካባቢ ጥበቃ መርሆዎችንና ህጎችን በተከተለ መልኩ ማከናወኑን በማረጋገጥ በሥራው ዙሪያ የሚታዩ የአሠራር ችግሮች ወይም ክፍተቶች ካሉ በመለየት ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦችን ማቅረብ ነው፡፡

**ለአካባቢ ክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ**

14. ለኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ (Audit Area) "የኢንዱስትሪ ፓርኮች የተቀናጀ የደረቅ እና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን መገምገም" የሚል ነው፡፡

## የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች

15. ለተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Audit Area) የኦዲቱን ዓላማ ለማሳካት በኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ስር የሚገኙ የኢንዱስትሪ ፓርኮች የደረቅ እና ፈሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት ውጤታማነትን በተመለከተ አራት ዋና የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) የተለዩ ሲሆን እንደሚከተለው ተቀምጠዋል፡፡ እነሱም፡-

- ኮርፖሬሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ያሉት ኢንዱስትሪዎች የሚያመነጩት ደረቅ እና ፈሳሽ ቆሻሻ በተገቢው መንገድ ለመሰብሰብ ለማስወገድ እና መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያግዙ የማስፈፀሚያ መመሪያዎች፣ማኑዋሎች እና ደረጃዎች መዘጋጀታቸውን እንዲሁም የአሰራር ስርአት መዘርጋቱንና ተግባራዊ ስለመደረጉ ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን ማጣራት
- ኮርፖሬሽኑ ኢንዱስትሪ ፓርኮችን ሲገነባ የደረቅና የፍሳሽ ማስወገጃ ሁኔታዎችን ባገናዘበ መልኩ ዲዛይን ማድረጉንና ቦታዎችን ማዘጋጀቱን ማጣራት ፣
- ኮርፖሬሽኑ የኢንዱስትሪ ፓርኮች የስራ ቦታና ግቢ በሰራተኞች ድህንነትና ጤንነት ላይ አደጋ የማያስከትል መሆኑን መገምገም፡፡
- ኮርፖሬሽኑ የአካባቢ ደህንነትን በጠበቀ መልኩ ስራውን እንዲሰራ ከሚያግዙት ባለ ድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበት የአሰራር ስርአት የዘረጋ እና የተደራጀ የመረጃ አያያዝ መኖሩን መገምገም ፣

የሚሉት ናቸው፡፡

### የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

16.ከላይ የተለዩት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ 26 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት የኮርፖሬኑን የመቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 326/2007፣ የኢንዱስትሪ ፓርኮች አዋጅ ቁጥር 886/2007፣ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ደንብ ቁጥር 417/2009 ፣የአደገኛ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አዋጅ ቁ.1090/2010 ፣የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ ቁ.513/1999፣የኢንዱስትሪ ብክለት መከላከያ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁ.159/2001፣የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁ.299/1995፣ ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ የየዓመቱ ዕቅድ እና ዕቅድ አፈፃፀሞችን (ከ2011-20014 ዓ/ም)፣ የተለያዩ መመሪያዎችን፣ ጥናቶችን፣ የስራ አመራር እና የቦርድ ቃለ ጉባኤዎችን በመከለስ ነው፡፡የተዘጋጁትም የመመዘኛ መስፈርቶች ለኮርፖሬሽኑ ተልከው አስተያየት እንዲሰጥበት የተደረገ ሲሆን በቀረቡት የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች ላይ አስተያየታቸውን በመስጠት ኦዲቱ እንዲቀጥል ፍላጎት እንዳላቸው ገልፀዋል፡፡ **የመመዘኛ መስፈርቶቹ (በአባሪ 4) ተያይዘዋል፡፡**

## የአካባቢ ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

### የአካባቢ ኦዲቱ ወሰን

17.ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ሲሆን በኢትዮጵያ የክዋኔ የኦዲት ስታንዳርድ እንዲሁም ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ የአካባቢ ክዋኔ ኦዲቱ የሸፈነው ከ2012 እስከ 2015 1ኛ ሩብ በጀት ዓመት ድረስ ያለውን የኢንዱስትሪ ፓርኮች የደረቅ እና የፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ በተመለከተ በኮርፖሬሽኑ የተከናወኑ ዋና ዋና ስራዎችን ይሸፍናል፡፡

### የአካባቢ ኦዲቱ ዘዴ

18.ዝርዝር የአካባቢ ኦዲቱ የተከናወነው የኮርፖሬኑን የመቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 326/2007 ፣ የኢንዱስትሪ ፓርኮች አዋጅ ቁጥር 886/2007 ፣ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ደንብ ቁጥር 417/2009 ፣የአደገኛ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አዋጅ ቁ.1090/2010 ፣የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ ቁ.513/1999 ፣የኢንዱስትሪ ብክለት መከላከያ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁ.159/2001፣የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁ.299/1995፣ ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ የየዓመቱ ዕቅድ

እና ዕቅድ አፈፃፀሞችን (ከ2011-20014 ዓ/ም)፣ የተለያዩ መመሪያዎችን፣ ጥናቶችን፣ የስራ አመራር እና የቦርድ ቃለ ጉባኤዎችን በመከለስ እንዲሁም በተመረጡ አራት ከተሞች ማለትም በአዲስ አባባ፤ድሬደዋ፤አዳማ እና ሀዋሳ ከተሞች በመገኘት እና በኢንዱስትሪ ፓርኮቹ ለሚመለከታቸው የስራ ሀላፊዎችና በከተማው የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በመጠየቅ፤ የቀረቡ ተያያዥነት ያላቸውን ማስረጃዎችን በመሰብሰብ፤እንዲሁም የመሰክ ምልከታ በማድረግ ነው፡፡(መጠይቅ የቀረበላቸው አካላት በአባሪ- 5 ተያይዟል)

# ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

### የኢንዱስትሪ ፓርኮች ሲገነቡ የአካባቢና የማሕበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ ሪፖርት ቀርቦ ተገምግሞ ፈቃድ የተሰጣቸው ስለመሆኑ በተመለከተ፤

19. ኮርፖሬሽኑ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ሲገነቡ የአካባቢና የማሕበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ ሊያደርጉና በሚመለከታቸው ስልጣን የተሰጣቸው ተቆጣጣሪ መ/ቤቶች ተገምግሞ ፈቃድ የተሰጣቸው ስለመሆኑ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

20. የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁ.299/1995 ክፍል ሶስት አንቀፅ 7/1 ላይ አንድ የፕሮጀክት ባለቤት የፕሮጀክቱን የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አካሂዶ የፕሮጀክቱን አሉታዊ ተፅዕኖዎች በቅድሚያ ለይቶና ተፅዕኖዎቹን የማስቀሪያ ወይም የመቋቋሚያ ዘዴን በጥናቱ ውስጥ አካትቶ ለሚመለከተው አካል ማቅረብ እንዳለበት ቢገልጽም

21. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት እንደታየው፡-

- ኢንዱስትሪ ፓርኮች ሲቋቋሙ የተጠናላቸው የአካባቢዊ እና የማህበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ (ESIA- Environment and Social Impact Assessment) ጥናት ማዕከላዊ በሆነ መልኩ ለቴክስታይልና ጋርመንት ዘርፍ የተጠና ቢሆንም በኢንዱስትሪ ፓርኮቹ ውስጥ ገብተው የማምረት ስራ የጀመሩ ፋብሪካዎች ግን ጥናቱ የማያካትታቸው ዘርፎች ማለትም የቀለም ፋብሪካ፣ ማዳበሪያ (የሲሚንቶ ከረጢት) ማምረቻ፣ ፕላስቲክ (ለታሸገ ውሃ ግብአት) የሚሆን ማምረቻ፣ የኮቪድ 19 ቴስት ኪት ማምረቻ የመሳሰሉት ፋብሪካዎች የሚገኙ መሆኑ፤
- በተጨማሪም ኮርፖሬሽኑ በአዲስ አበባ ፣አዳማ ፣ድሬዳዋ እና ሐዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ለሚገኙ 46 ፋብሪካዎች የአካባቢና ማህበራዊ አስተዳደር ዕቅድ (Environmental and Management Plan) እንዲያዘጋጁ በደብዳቤ ያሳወቀ መሆኑን ከቀረበ መረጃ ለማወቅ ቢቻልም፣ 9 ፋብሪካዎች ብቻ ዕቅዱን አዘጋጅቶ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ያፀደቁ ሲሆን፣ 37 ፋብሪካዎች ሌሎች ግን ምላሽ ያልሰጡ መሆኑን፤

በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ ኢንዱስትሪ ፓርኮችና ከሰነድ ክለሳ ለማወቅ ተችሏል።

22. ስለጉዳዩ የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ፣ እንዲሁም ለኮርፖሬሽኑ በተላከው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ወቅት በሰጡት ምላሽ፡-

- ❖ ምንም እንኳ ኢንዱስትሪ ፓርኮቹ ሲቋቋሙ ለጨርቃ ጨርቅ እና ጋርመንት ተብሎ ቢሆኑም በሀገሪቱ ውስጥ በነበረው ነባራዊ ሁኔታ ባለሀብቶች በሚፈለገው መጠንና ቁጥር ሊመጡ ባለመቻላቸው ከፍተኛ ኢንቨስትመንቶች የተደረገባቸው ኢንዱስትሪ ፓርኮች ጥቅም ሳይሰጡ ማስቀመጥ አግባብ ስላልሆነ፣ አነስተኛ ተፅዕኖ ያላቸውን ሌላ ዘርፎች ፓርኮች ውስጥ ገብተው እንዲሰሩ ጥረቶች እየተደረጉ ያሉ በመሆኑ እና ኢ/ፓርኮች ውስጥ ገብተው የሚሰሩ ባለሃብቶች በምርት ሂደታቸው በአካባቢ ላይ ተፅዕኖ እንዳያሳድሩ የራሳቸውን የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ አዘጋጅተው ተግባራዊ እንዲያደርጉ በተደረሰ መግባባት መሠረት 15 ባለሃብቶች የራሳቸውን አማካሪ ድርጅት በመለየት ዝግጅት የጀመሩ ሲሆን የተቀሩት አማካሪ በመለየት ሂደት ላይ የሚገኙ መሆኑን፤
- ❖ በተጨማሪ ኮርፖሬሽኑ የሃገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ ከግምት በማስገባት በኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች አገልግሎት ኢንዱስትሪ ፓርኮች ከጨርቃ ጨርቅ እና ጋርመንት ዘርፍ ውጭ ሌላ ለምን አገልግሎት መስጠት እንደሚችሉ የሚያመላክት ጥናት (re-purposing/ specialization of industrial park study) በማከናወን ላይ እንደሚገኝ፥

ገልጸዋል።

23. የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ይህን ይበሉ እንጂ፡- የአካባቢያዊ እና የማህበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት ሳይጠናላቸው ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮቹ ውስጥ ከጨርቃ ጨርቅና ጋርመንት ውጪ የሆኑ አነስተኛ ተፅዕኖ ያላቸውን ሌሎች ዘርፎች ፓርኮች ውስጥ ገብተው እንዲሰሩ ማድረጉን ቢገልፅም ፋብሪካዎቹ ወደ ስራ ከመግባታቸው በፊት የአካባቢና ማህበረሰብ ተጽዕኖአቸው አነስተኛ ስለመሆኑ የቀረበ ጥናት ያለመኖሩ፣ የአካባቢና ማህበራዊ አስተዳደር ዕቅድ እንዲያዘጋጁ በደብዳቤ መግለፁ መልካም ቢሆንም፣ በአዲስ አበባ ፣አዳማ ፣ድሬዳዋ እና ሐዋሳ ኢ/ፓርኮች ውስጥ የሚገኙ 37ቱ ፋብሪካዎች ምላሽ ያልሰጡ በመሆኑ ምክንያት የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡
24. በመሆኑም የልማት ሃሳብ ንድፍ ሲዘጋጅ፣ ቦታው ሲመረጥ፣ ሲገነባ ወይም ሲተገበር የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ሳይጠና የልማት ፕሮጀክቱ ወደ ትግበራ ከተገባ ከሚያስገኘው ዘርፈ ብዙ ጥቅሞች በተቃራኒው አካባቢውን ለብክለት ተጋላጭ ሊያደርግ እና በሰው ጤና ወይም ደህንነት፣ በዕፅዋት፣ በእንስሳት፣ በአፈር፣ በአየር፣ በውሃ አካላት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያስከትል ይችላል፡፡

**በኢንዱስትሪ ፓርኮች የዝቃጭ አያያዝና አወጋገድ ስርአትን በተመለከተ፡**

25.ኮርፖሬሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚመነጨውን ዝቃጭ በተመለከተ የዝቃጭ አያያዝና አወጋገድ ስርአት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

26. ለቦሌ ለሚ እና ቂሊንጦ ኢንዱስትሪያል ፓርኮች በተዘጋጀው የዝቃጭ አስተዳደር መመሪያ ገፅ 27 ላይ (Sludge Management Guideline For Bole Lemi and Kilinto Industrial Parks) ኢንደስትሪ ፓርኩ ሥራ በሚሠራበት ወቅት በቦታው ላይ ያለውን የዝቃጭ አያያዝ ሂደት ኦዲት ሊያደርግ እንደሚገባ ይገልፃል።

27.ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት እንደታየው፡-

- በኢንዱስትሪ ፓርኮች ከፍሳሽ ማጣሪያ የሚወጣ ዝቃጭ (በተለይ በሐዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ) ለረጅም ጊዜ በኢንዱስትሪ ፓርኩ ግቢ ውስጥ ለዝናብ በተጋለጠ ሁኔታ ከ5 ዓመታት በላይ ተከማችቶ (በከፊል ሼድ ውስጥ፣ በኮንቴነር፣ በአሮጌ የማደበሪያ ጆንያዎች ተደርጎ በተለያዩ ቦታዎች) እንደሚገኝና በዝናብ ወቅትም እየታጠበ ከዝናብ ፍሳሽ ጋር እንደሚወርድ እንዲሁም የግቢውን ውበት እያበላሸ መሆኑ፤



**ፎቶ ቁጥር 1. በሐዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ ዝቃጩ የዝናብ ውሃ መውረጃ ቦይ አጠገብ ተከማችቶ የሚያሳይ**



ፎቶ ቁጥር 2. በሐዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ በሼድ (ማምረቻ አዳራሽ) ውስጥ እና ከውጭ ዝቃጭ ተከማችቶ የሚያሳይ

- ❖ በሀዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ ለዝቃጭ ማድረቂያ ከፍተኛ ማሽነሪ ከፍሳሽ ማጣሪያው ጋር የተቋቋመ ቢኖርም፤ ማሽነሪው መስራት እየቻለ ዝቃጭ የማድረቁ ሂደት በጸሐይ ኃይል እንዲሆን እና ለማድረቂያ የተዘጋጀ ቦታም ሳይኖር በግቢው የመተላለፊያ መንገድ ላይ ተበትኖ በጸሐይ ኃይል በሚደርቅበት ወቅት በንፋስ ኃይል እየተበተነ የአካባቢ ብክለት እያስከተለ መሆኑን፤

በኦዲቱ ወቅት በመስክ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡



ፎቶ ቁጥር 3. በሐዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ ዝቃጩ መንገድ ላይ ተበትኖ ሲደርቅ

28.ስለጉዳዩ የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃል መጠይቅ፣ እንዲሁም ለኮርፖሬሽኑ በተላከው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ፡-

- ኮርፖሬሽኑ የዝቃጭ አስተዳደር መመሪያ ማዘጋጀትና መተግበር እንዲሁም የደረቅ ዝቃጭ መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚቻልባቸውን ሁሉንም አማራጮች በማስጠናት፤ እንዲሁም በሀገሪቱ ዝቃጭን መልሶ የመጠቀምና ማስወገድ ደረጃ እንዲወጣና ተግባራዊ እንዲደረግ ውጤታማ ሥራ የሰራ መሆኑን፤
- ከላይ ተገለፁት ቅድመ ሁኔታዎች እስኪሟሉ ድረስ የነበረውን ዝቃጭ ሃላፊነት በተሞላው መልኩ ለማከማቸት ጥረት በማድረግ ዝቃጭን በማዳበሪያ ቋጥሮ በኮንቴነር ውስጥ ማስቀመጥ፣ ጂኦ-ሜምብሬን (Geo-membrane) አንጥፎ ማድረቅና ማከማቸት ተገቢነት ያለውና በወቅቱ አስፈላጊም እርምጃ እንደ ነበር፤ መመሪያዎች እና አሠራሮች ከተዘጋጁ በኋላ ግን ደረጃ በደረጃ የዝቃጭ አያያዝና አወጋገድ አሰራሩ መቀየሩን፤
- ሃገራዊ የስለጅ ደረጃ መውጣቱን ተከትሎ ዝቃጩን በአካባቢ ተቀባይነት ባለው ሁኔታ መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል እና ለማስወገድ ከባለድርሻ አካላት ጋር በተደረገ ጥረት ዝቃጭን በሌሎች ኢንዱስትሪዎች በተለይም ለመሬት ንጣፍ (Paver Block) ማምረቻ ግብአትነት እንዲውል እንዲሁም ከፍተኛ ጥቅም የሚያስገኝ የፈሳሽ ማዳበሪያ ስራ እንዲውል እየተደረገ እንዳለ፤
- በዚሁ መሰረት ዝቃጭ በዝናብ ታጥቦ እና ተጠርጎ ወደ ሀይቅ የሚሄድ ዝቃጭም (ስለጅ) አለመኖሩን እንዲሁም በሪፖርቱ የተገለፀው ዝቃጭ በየቦታው መታየት ለጊዜው የነበረ ሲሆን አሁን ላይ ግን ለተለያዩ ጥቅሞች ዝቃጩን በማዋል ለችግሩ ዘላቂ መፍትሄ ለመስጠት ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ መሆኑን፤

- ዝቃጩን (ስለጅን) በማሽንም ሆነ በቀጥታ በፀሃይ ሀይል በሚደርቅበት ወቅት የማድረቅ መርህ (Principle) ተመሳሳይ እርጥበትን በማትነን (Moisture Evaporation) ሲሆን፤ የማድረቅ ሂደቱ በተለየ መልኩ በአካባቢ ላይ የሚያመጣበት ጉዳት አለመኖሩን፤ ዝቃጩን (ስለጅን) ማድረቅ ሳይቻል ከነእርጥበቱ ታሽጎ የሚቀመጥ ከሆነ በሚፈጥረዉ ላቦት ምክንያት ለአካባቢ ጠንቅ እንዳይሆን ታሳቢ በማድረግ፤ ዝናብ በሌለበት ወቅት ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ የኮንክሪት (Concrete) አስፓልትን በጊዜያዊነት ለስለጅ ማድረቂያነት እንዲውል መደረጉን፤

❖ በፍሳሽ ማጣሪያዉ ጊቢ ውስጥ የተተከለው የዝቃጭ (ስለጅ) ማድረቂያ ማሽን (Electrical Sludge Dryer) ለኢንዱስትሪ ፓርኩ በነፃ የተሰጠ ቢሆንም ማሽኑ ከሚጠቀመዉ ሃይል እና ከሚያድርቀዉ የዝቃጭ (ስለጅ) መጠን ጋር ሲነፃፀር ፓርኩን ለከፍተኛ ወጭ የሚዳርግ በመሆኑ አዋጭ አማራጭ ማድረቂያ ዘዴን መከተል አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱን፡፡ በዚሁ መሠረት ማሽኑን በክረምት ወቅት እየተጠቀሙበት እንደሚገኙ ፤

ገልጸዋል፡፡

29.የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ይህን ይበሉ እንጂ፡-

❖ ዝቃጩን (ስለጁን) በሜዳ ላይ የጎርፍ መውረጃ ቦይ አጠገብ ለረጅም ጊዜ ተከማችቶ ለዝናብ ተጋላጭ በሆነ መልኩ፣ (በከፊል ሼድ ውስጥ፤ በኮንቴነር፤ በአሮጌ የማደበሪያ ጆንያዎች ተደርጎ በተለያዩ ቦታዎች) የሚገኝ መሆኑ፤በዝናብ ወቅትም እየታጠበ ከዝናብ ፍሳሽ ጋር እንደሚወርድ፤እንዲሁም የግቢውን ውበት እያበላሸ መሆኑ፤

❖ ስለጅን መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል በሂደት ያሉት ምርምርና ጥረቶች ገና በተግባር ያልዋሉ በመሆኑ፤

❖ ዝቃጩን (ስለጅን) በማሽንም ሆነ መተላለፊያ መንገድ ላይ በማስጣት በቀጥታ በፀሃይ ሀይል በሚደርቅበት ጊዜና ከደረቀ በኋላም ክፍት ቦታ/አስፋልት ላይ በመሆኑ የዝቃጩ ብናኝ በንፋስ ኃይል ወደ አየር ሊበተን ስለሚችል በአካባቢና በሰው ላይ ጉዳት ሊያደርሱ ስለሚችል የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

30.በመሆኑም በሁሉም ኢንዱስትሪ ፓርክ ግቢ ውስጥ የሚገኘው ዝቃጭ (ስለጅ) የሚወገድበት ወይም በጥናት ጥቅም ላይ የሚውልበት መንገድ ካልተፈለገ የግቢውን ውበት ከማበላሸት በተጨማሪ በዝናብ ወቅት እየታጠበ ከዝናብ ፍሳሽ ጋር በመውረድ በአካባቢው ላይ ብክለት ሊያስከትል እንዲሁም በፀኃይ ሀይል በሚደርቅበት ሂደትና ከደረቀ በኂላም በብናኝ መልክ በንፋስ ሀይል ወደ አካባቢው አየር በመግባት አካባቢውን የሚበክል ሲሆን ይህም በሰውና ህይወት ባላቸው ፍጥረታት ላይ ችግር ሊፈጥር ይችላል፡፡

## የአረንጓዴና የጋራ ቦታዎች እንክብካቤ ልማት ተግባራዊነት እና ከፓርኮቹ የሚመነጩ ቆሻሻዎች አያያዝ ስልቶች ክትትል መደረጉን በተመለከተ

31.ኮርፖሬሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች የአረንጓዴና የጋራ ቦታዎች እንክብካቤ ልማት ተግባራዊ መደረጉን እንዲሁም ከኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚመነጩ ቆሻሻዎችን የመቀነስ፤ እንደገና

የመጠቀም፤ መልሶ ለሌላ ምርት ግብዓትነት የማዋል ስልቶች መተግበራቸውን ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

32. ስለ ኢንዱስትሪ ፓርኮች የወጣ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁ. 417/2009 አንቀጽ 13/ረ ላይ የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ የፈሳሽና ደረቅ ቆሻሻ አወጋገድን ጨምሮ የጋራ ቦታዎች ጽዳት የመጠበቅ ሃላፊነት እንዳለበት ይገልጻል፡፡

33. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት እንደታየው፡-

❖ በሐዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ ያሉት የተወሰኑ አረንጓዴ ስፍራዎች እና በተለያዩ የአጥር ጥግ ቦታዎች በርካታ መጠን ያለው የዝቃጭ ማጠራቀሚያ ማዳበሪያ ወይም ከረጢቶች መጣያ መሆናቸው እና የተወሰኑ አረንጓዴ ስፍራዎች ላይ ደግሞ ከፍሳሽ ማጣሪያ የወጣ የደረቅ ዝቃጭ (ቆሻሻ) ተበትኖባቸው የሚገኝ መሆኑ፤በተደረገው የመስክ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡



ፎቶ ቁጥር 4. አረንጓዴ ስፍራዎች የዝቃጭ ማጠራቀሚያ የነበረ አሮጌ ማዳበሪያ (ከረጢት) መጣያ መሆናቸው በከፊል

❖ በድሬዳዋ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውሺ ነምበር ዋን ኮተን ኢትዮጵያ ቴክስታይል የተባለው ድርጅት ግቢ ውስጥ ተረፈ ምርት (ቆሻሻ) ከአራት ወራት በላይ ተከማችቶ እንደሚገኝ እና ከፋብሪካውም በሚወጣ ብናኝ የግቢው ውበት እየተበላሸ መሆኑ በመስክ ምልከታ ለማየት ተችሏል፡



**ፎቶ ቁጥር 5. የውሺ ነምበር ዋን ኮተን ኢትዮጵያ ቴክስታይል ተረፈ ምርት ሳይወገድ ለረዥም ወራት ግቢው ውስጥ በየቦታው ተጥሎ እንዲሁም ብናኙ የግቢውን ውበት እያበላሸ መሆኑን የሚያሳይ**

34. ስለጉዳዩ የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ፣ እንዲሁም ለኮርፖሬሽኑ በተላከው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ፡-

- ❖ አሁን ላይ የዝቃጭ ማጠራቀሚያ ማዳበሪያ በየቦታው ተጥሎ የማይገኝ መሆኑን፡፡ በአሁኑ ወቅት በ27 ብር አንድ ማዳበሪያ ይገዛ የነበረውን ዝቃጩን (ስለጁን) በማድረቅ የተገኘውን ትርፍ ማዳበሪያ መልሰው በመጠቀም ለ1 ዓመት ከ2 ወር ማዳበሪያ ግዥን ማስቀረት መቻላቸውን፤ በሌላ በኩል ደግሞ የተቀዳደ ባዶ ማዳበሪያ ለባዮ-ማስ ኢነርጂ ምንጭነት በመጠቀም ወደ ከተማ ደረቅ ቆሻሻ ቦታ እንዳይሄድና እንደ ኃብት እንዲቆጠር በማድረግ ማስተካከያ መወሰዱን፤ ይኸውም ለፓርኩ እንደ ምርጥ ተሞክሮ ሊወሰድ የሚችል ጉዳይ መሆኑን፤
- ❖ በተጨማሪም በፀደቀው ሀገር አቀፍ የዝቃጭ (ስለጅ) ስታንዳርድ መሰረት ተጠንቶና ተገቢው ጥንቃቄ ተደርጎ ዝቃጭ (ስለጅ) ለአረንጓዴ ቦታ ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን፤ አሁንም በስታንዳርዱ መሰረት የተፈቀደ ተግባር በመሆኑ የፓርኩ አረንጓዴ ቦታ የኮምፖስት ፍላጎት እየታየ እየተተገበረ የሚገኝ መሆኑን፤ አሰራሩን በማዘመን ከዝቃጭ (ስለጅ) ፈሳሽ ማዳበሪያ ለማዘጋጀት በሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ ተመራማሪዎች ሙከራ እየተደረገ መሆኑን፤

❖ ውሺ ነምበር ዋን ኮተን ኢትዮጵያ ቴክስታይል የተባለው ድርጅት በድሬደዋ ነፃ ንግድ ቀጠና የሚገኝ የግል አልሚ ድርጅት ሲሆን፤ የማምረቻ መሰረተ ልማቶች በሙሉ የተገነባው በድርጅቱ መሆኑና እንደተባለውም ከጥጥ ተረፈ ምርት ጋር በተያያዘ የተከሰቱ ችግሮች የሚያውቋቸው እንደሆነ እና ድርጅቱ ተረፈ-ምርቶቹን በተገቢዉ መንገድ የሚያስወግድበት ሁኔታ በማመቻቸት በአጭር ጊዜ ውስጥ ችግሩን እንዲፈታ በቃልም ሆነ በደብዳቤ የተገለፀለት መሆኑን፤

ገልጸዋል፡፡



ፎቶ ቁጥር 6. የዝቃጭ መያዣ የነበሩ ማዳበሪያዎች (ከረጢቶች) ከተከማቹበት ኮንቴይነሮች ተዘርግፈው የሚያሳይ

35.የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ይህን ይበሉ እንጂ፡-

❖ በኦዲቱ ወቅት የተወሰኑ አረንጓዴ ስፍራዎች እና በተለያዩ የአጥር ጥግ ቦታዎች ላይ በርካታ መጠን ያለው የዝቃጭ ማጠራቀሚያ ማዳበሪያ ወይም ከረጢቶች መጣያ መሆናቸው እና ግቢው ውስጥ ካሉ በርካታ የዝቃጭ (ስለጅ) መያዥያ ከረጢት ከሞላባቸው ኮንቴይነሮች ተከፍተው በየሜዳው ተዘርግፎ የሚገኙ አሮጌ ከረጢቶች የሚታዩ መሆኑ እንዲሁም በፀደቀው ሀገር አቀፍ የዝቃጭ (ስለጅ) ስታንዳርድ መሰረት ተጠንቶና ተገቢው ጥንቃቄ ተደርጎ ዝቃጭ (ስለጅ) ለአረንጓዴ ቦታ ተግባራዊ የተደረገ መሆኑ ቢገለፅም በስለጅ ስታንዳርዱ መሰረት የተጠናው ጥናት ያልቀረበ በመሆኑና የተወሰኑ አረንጓዴ ስፍራዎች ላይ ከፍሳሽ ማጣሪያ የወጣው የደረቀ ዝቃጭ (ቆሻሻ)

ተበትኖባቸው የሚገኝ ስለመሆኑ በመስክ ምልከታ ወቅት የታየ በመሆኑ ምላሻቸውን አልተቀበልነውም፡፡

36. በመሆኑም በአረንጓዴ ስፍራዎቹ ተከማችቶ የሚገኘው የዝቃጭ (ቆሻሻ) መያዣ ባዶ ከረጢቶች ላይ የሚረግፈው ዝቃጭ በአረንጓዴ ስፍራዎቹ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያደርስ እና ከኮንቴይነሮቹ ላይ ተዘርግፈው የሚገኙት ማዳበሪያዎች(ከረጢቶች) የዝቃጭ (ስለጅ) ማጠራቀሚያ የነበሩ በመሆኑ በአካባቢው ላይ ብክለት ሊያስከትሉ እንዲሁም ኮርፖሬሽኑ ውሺ ነምበር ዋን ለተሰኘው ፋብሪካ ተረፈ ምርቱን በአግባቡ እንዲያስወግድ በቀን 02/03/2014 በቁጥር DDIP/150/2014 እና በቀን 17/03/2014 በቁጥር DDIP/165/2014 ደብዳቤ የፃፈ ቢሆንም ቀጣይነት ያለው ክትትል ባለመደረጉ ምክንያት ችግሩ የኦዲት ቡድኑ ለመስክ ምልከታ በፋብሪካው በተገኘበት ማለትም በህዳር ወር 2015 ዓ.ም ድረስ የነበረና ያልተቀረፈ በመሆኑ ይህ ተረፈ ምርት የሚወገድበትን ወይም ጥቅም ላይ የሚውልበትን አሰራር ካልተዘረጋ ቆሻሻው በምርት ሂደት እየጨመረ የሚሄድ በመሆኑ የፋብሪካው ውበት ከማበላሸት በዘለለ የማምረት ሂደቱን ሊያስተጓጉልና ለኢንዱስትሪ ፓርኩም የፅዳት ስጋት ሊሆን ይችላል፡፡

## ከፍሳሽ ማከሚያዎች የሚመነጭን ዝቃጭ ቆሻሻ ለማስወገድ በዕቅድ ተይዞ የሚተገበር እና የሳኒተሪ ላንድ ፊል መዘጋጀቱን በተመለከተ

37. ኮርፖሬሽኑ በፓርኮች ውስጥ ያለውን የዝቃጭ አያያዝና አወጋገድ በዕቅድ በመያዝ ኦዲት ሊያደርግና ዝቃጩ (Sludge) አካባቢያዊና ማህበራዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ ለማስወገድ የሚሆን ቦታ (የሳኒተሪ ላንድ ፊል) በዲዛይኑ ውስጥ አካቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ለቦሌ ለሚ እና ቂሊንጦ ኢንዱስትሪያል ፓርኮች በተዘጋጀው የዝቃጭ አስተዳደር መመሪያ ገፅ 27 ላይ የኢንደስትሪ ፓርኮች የዝቃጅ (Sludge) አስተዳደር በእቅድ ይዘው በትክክል መተግበር እንዳለባቸው እንዲሁም፤ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ከ2008-2012 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ገፅ 70) ላይ ከፍሳሽ ማከሚያዎች የሚመነጭን ዝቃጭ አካባቢያዊና ማህበራዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ ለማስወገድ ለሳኒተሪ ላንድ ፊልድ ግንባታ የሚሆን ቦታ ለፓርክ መገንቢያ የሚሆን ቦታ ሲመረጥ ዲዛይንና ግንባታው አብሮ ታሳቢ መደረግ እንዳለበት ይገልፃል፡፡

38. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

❖ በኢንዱስትሪ ፓርኮች የዝቃጭ አስተዳደር ዕቅድ በመያዝ ዝቃጩን ለማስወገድ የተደረጉ ጥረቶች ቢኖሩም ፤ በመስክ እይታ ወቅት ግን ዝቃጩ በየቦታው ተከማችቶ የሚገኝ መሆኑን በሰነድ ክለሳ እና በመስክ ጉብኝት ለማየት ተችሏል፡፡

❖ በሃዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ የሚገኘው ዝቃጭ አዲስ አበባ ወደሚገኘው ረጲ ከቆሻሻ ሃይል ከሚያመነጨው ተቋም ጋር በመነጋገር ዝቃጩን ወደ አዲስ አበባ በማጓጓዝ ወደ ሃይል ለመቀየር ለአንድ ዓመት ይላክ እንደነበርና አሁን ላይ ግን ይህ የተቋረጠ መሆኑ ፣

❖ እንዲሁም በናሙና ተመርጠው በታዩት አራት ኢንዱስትሪ ፓርኮች ከፍሳሽ ቆሻሻ ማከሚያዎች የሚመነጭን ዝቃጭ ቆሻሻ (Sludge) አካባቢያዊና ማህበራዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ ለማስወገድ የሚሆን ቦታ(የሳኒተሪ ላንድ ፊል) በዲዛይናቸው ውስጥ በማካተት እና ቦታውን በማዘጋጀት አገልግሎት እንዲሰጥ ያላደረጉ መሆኑን በሰነድ ክለሳና በመስክ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡

39.ስለጉዳዩ የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ፣ እንዲሁም ለኮርፖሬሽኑ በተላከው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ፡-

✓ በኮርፖሬሽኑ አመታዊ ዕቅድ ላይ በየፓርኩ የሚወገድ የዝቃጭ መጠን በእቅድ የሚያዝ ሲሆን ስለጁን ለማስወገድ የሚያስፈልግ በጀት በየፓርኮቹ እንዲያዝ እንደሚደረግ እና በዚሁ አግባብ የቀን ተቀን ሥራውም ታቅዶ የሚሰራ መሆኑን፤

✓ ስለጅ በዝቅተኛ ዋጋ መልሶ የመጠቀም አማራጮች እስካሉ ድረስ ስለጅን ወደ አዲስ አበባ ኃይል ማመንጫ መላክ የግድ እንደሆነ የተወሰደው ግንዛቤ ስለጅን መልሶ ለመጠቀም እየተደረጉ ያሉ ጥረቶችን በዜሮ የሚያባዛ መሆኑን፡፡ በዚሁ መሰረት ስለጅን መልሶ የመጠቀም ፕሮጀክቶቻቸውን በሙሉ በቀጣይ አሟጠው በመተግበር ስለጁን ወደ ሀብትነት የመቀየር ስራውን እንደሚሰሩ፤ ጥቅም ላይ የማይውለውን ስለጅ ደግሞ በሀገሪቱ ህግ እንዲወገድ እንደሚያደርጉ፡

✓ በተጨማሪም ኮርፖሬሽኑ ከፍሳሽ ማጣሪያዎች የሚመነጭ ስለጅ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ የሳኒተሪ ላንድ ፊል በሃዋሳ እና ኮሞቦልቻ በመገንባት ለማስወገድ የአካባቢ እና የማህበራዊ የተፅዕኖ ግምገማ ጥናት አስጠንቶ ፈቃድ ቢያገኝም ይህ እርምጃ ከኢኮ-ኢንዱስትሪ ፓርክ መርህ አንፃር የመጨረሻ አማራጭ በመሆኑና አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታም የCircular Economy ፅንሰ ሃሳብ በአለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን ተከትሎ ኮርፖሬሽኑ በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ለመሆን ከአለም አቀፍ ነባራዊ ሁኔታ ጋር እራሱን ማስታረቅ ያለበት በመሆኑ የሳኒተሪ ላንድ ፊል ግንባታን

ለጊዜው እንዲዘገይ እና ዝቃጩን (ስለጅን) መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል የተለያዩ ጥረቶችን እያደረጉ የሚገኙ መሆኑን፣

ገልፀዋል፡፡

40.የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ይህን ይበሉ እንጂ፡-

- የሳኒተሪ ላንድ ፊል በሃዋሳ እና ኮምቦልቻ በመገንባት ዝቃጩን ለማስወገድ የአካባቢ እና የማህበራዊ የተፅዕኖ ግምገማ ጥናት አስጠንተው ፈቃድ ያገኙ መሆኑን ቢገልፁም ይህን ባለመጠቀማቸው ዝቃጩ ለረዥም ጊዜ በኢንዱስትሪ ፓርኩ ግቢ ውስጥ በየቦታው ተከማችቶ የሚገኝና የሚያዘውም ዕቅድ በትክክል ተግባራዊ የማይደረግ መሆኑን ተከማችቶ የሚገኘውን ዝቃጭ በማየት መግለጽ የሚቻል በመሆኑ እና ኮርፖሬሽኑም ኢንዱስትሪ ፓርኮቹ ዝቃጩን እንዲያስወግዱ በክትትሉና ቁጥጥሩ ውስጥ አስገዳጅ እርምጃ የወሰደበት አግባብ ባለመኖሩ፣
- በሐዋሳ ኢ/ፓርክ የሚገኘውን ዝቃጭ አዲስ አበባ ወደሚገኘው ረጲ ከቆሻሻ ሃይል ከሚያመነጨው ተቋም ጋር በመነጋገር ዝቃጩን ወደ አዲስ አበባ በማጓጓዝ ወደኃይል ለመቀየር ይላክ የነበረው በመቋረጡ ምክንያት እና በሃላፊዎቹ እንደተባለው ዝቃጩን ወደ ሃብትነት የመቀየር ሂደቱ ባለመተግበሩ በመስክ ጉብኝት ወቅት ዝቃጩ በየቦታው ተጠራቅሞ የሚገኝ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል።

41.በመሆኑም በኢንዱስትሪ ፓርኩ ዝቃጭን በተመለከተ በየዓመቱ ለማስወገድ የሚይዘው ዕቅድ በትክክል ተግባራዊ የማይደረግ ከሆነ ኢንዱስትሪ ፓርኩ የሚያመነጨውን ዝቃጭ በየጊዜው እንዲወገድ ለማድረግ ወይም ጥቅም ላይ የሚውልበትን መንገድ ካልተመቻቸ ወይም በጥናት ለሌላ ስራ እንደግብአት የሚውልበት ዘዴ በተጨባጭ ካልተፈለገለት በጊዜ ሂደት የፓርኩን ስራ ሊያስተጓጉልና አምራቾቹም ላይ የጤና ችግር ሊያደርስ ብሎም አካባቢውንም ለብክለት ሊዳርግ ይችላል፡፡

## በኢንዱስትሪ ፓርኮች ቆሻሻን ለማስተዳደር የሚያስችል ስርአት ተዘርግቶ ክትትል መደረጉን በተመለከተ

42.ኮርፖሬሽኑ በየኢንዱስትሪዎቹ ቆሻሻን ለማስተዳደር የአሰራር ስርአት መዘርጋቱን እንዲሁም ተግባራዊ ስለመደረጉ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

43.ለኮርፖሬሽኑ በተዘጋጀው standard operation procedure page 25. ላይ ማንኛውም የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት በተደነገገው መሰረት የሚለቀው ቆሻሻ ውሃ የጋራ ማስወገጃ ቱቦን

በመጠቀም የሚያስወግድና ምንም አይነት ሌላ አማራጭ ወይም የፍሳሽ ማስወገጃ ዘዴዎችን አለመጠቀሙን ፓርኮቹ ሊቆጣጠሩ እንደሚገባ ይገልፃል፡፡

44. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ❖ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚገኙ ባለሃብቶች ለምሳሌ (ኪንግደም ኢትዮጵያ ላይነን ፒ.ኤል.ሲ፣ ኢንዶቹይን አፓረል ፒ.ኤል.ሲ የመሳሰሉት) መረጃ ለመስጠትና ፋብሪካቸውን ለኦዲት ስራ ክፍት ለማድረግ ፈቃደኛ አለመሆናቸው እና የአካባቢ ጥበቃ አካላትም ወደ ፋብሪካዎቹ ገብተው ክትትል ለማድረግ እየተቸገሩ መሆኑ፡
- ❖ በአዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ ስር የሚገኙት ኪንግደም ኢትዮጵያ ላይነን ፒ.ኤል.ሲ እና ሰንሻይን ኢትዮጵያ ውል ቴክስታይል ፒ.ኤል.ሲ እንዲሁም በቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ ስር የሚገኘው ሱፍሌት ብቅል ፋብሪካ ፍሳሻቸውን ወደ አካባቢ የሚለቁ መሆናቸውን በተለይ ሱፍሌት ብቅል ፋብሪካ ፍሳሹ ወደ ማሳ (እርሻ) የሚገባ እና ከማጣሪያውም መጥፎ ሽታ የሚወጣ መሆኑ፡፡



ፎቶ ቁ.7. በቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ ስር የሚገኘው ሱፍሌት ብቅል ፋብሪካ ፍሳሹ ወደ ማሳ ሲገባ የሚያሳይ



ፎቶ ቁ.8. በአዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ ስር የሚገኘው ሰንሻይን ኢትዮጵያ ፍሳሹ ወደ አካባቢው ሲፈስ የሚያሳይ



**ፎቶ ቁጥር** 9. በአዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ ስር የሚገኘው ኪንግደም ኢትዮጵያ ላይነን ፒ.ኤል.ሲ ፍሳሹን ወደ አካባቢው ሲለቅ የሚያሳይ

❖ ከሐዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ ለክረምት የጎርፍ ውሃ መሄጃ ተብሎ በተዘጋጀው የዝናብ ፍሳሽ ማስወገጃ (ካናል) ዝናብ በሌለበት ወቅት ማለትም በበጋ ቀለም እና መጥፎ ሽታ ያለው ውሃ እየፈሰሰ ቀጥታ ወደ ሐዋሳ ሐይቅ እየገባ መሆኑ በመስክ ምልከታ የታየ መሆኑ፤



ፎቶ ቁጥር 10. ከሐዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ እስከ ሐዋሳ ሐይቅ ድረስ በቀጥታ ተገናኝቶ በተገነባው የዝናብ ፍሳሽ ማስወገጃ (ካናል) አማካኝነት ፍሳሽ ወደ ሐይቁ ሲገባ

❖ በናሙና ተመርጠው በታዩ ኢንዱስትሪ ፓርኮች የአካባቢ ጥበቃ ባለሙያዎች ለየፓርኮቹ አንዳንድ በኮንትራት ተቀጥረው እየሰሩ የሚገኙ ሲሆን ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ስፋት እና በውስጣቸው ከሚገኙ ፋብሪካዎች ብዛት አንጻር በአንድ ባለሙያ በኢ/ ፓርክ ያሉትን ፋብሪካዎች በሙሉ ለመከታተልና ድጋፍ ለመስጠት አስቸጋሪ መሆኑ እና የኢንቫይሮመንት ቲም /ዩኒት/ በዘላቂነት ያልተቋቋመ መሆኑ፡

በመስክ ምልከታና በቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

45. ስለጉዳዩ የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ እና ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ፡-

✓ የትኛዉም አምራች ድርጅት ለአካባቢ ጥበቃ አካላትም ሆነ ፍቃድ ላለዉ የኦዲት ስራ ክፍት እንዲሆኑ በጽኑ የሚያምኑ መሆኑንና በተጠቀሱት ድርጅቶችም ሆኑ ሌሎች ድርጅቶች በአካባቢ ክዋኔ ኦዲት ላይ ለመተባበር ፍቃደኛ ካለመሆናቸው ጋር በተያያዘ ከድርጅቶች ጋር ግልፅ ውይይት በማድረግ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ እንደሚሰሩ፤

✓ ሰንሻይን እና ኪንግደም የተባሉት ድርጅቶች ፍሳሻቸውን ወደ ዉጪ ሳይሆን ወደ አዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ ማዕከላዊ ዜሮ ፍሳሽ ቴክኖሎጂ Zero Liquide Discharge (ZLD) ፍሳሽ ማጣሪያ የሚልኩ ሲሆን፤ ለዚህም በየወሩ በላኩት ፍሳሽ መጠን መሠረት የፍሳሽ ማጣሪያ

አገልግሎት ክፍያ እንደሚከፍሉ፡፡ ይሁንና በመስክ ምልከታ ታዩ የተባሉ ክፍተቶች ካሉ ተከታታይነት ያለው የቁጥጥር ስራዎች በመሥራት ችግሮች እንዲቀረፉ እንደሚደረግ፤ እንዲሁም ሶፍሌት ማልት የተባለዉ ድርጅት የራሱ የሆነ ፍሳሽ ማጣሪያ ያለዉ ሲሆን በህገ-ወጥ መንገድ ፍሳሹን ወደ ውጪ የሚለቅ መሆኑን ማስረጃ ላይ መሠረት በማድረግ የእርምት እርምጃ እንዲወሠድ እንደሚያደርጉ፤

- ✓ የሀዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ ፍሳሽ ማጣሪያ የዜሮ ፈሳሽ ቴክኖሎጂ (Zero Liquid Discharge) ፍሳሽ ማጣሪያ ሲሆን እያጣራ ያለውም በዚሁ መሰረት ሲሆን፤ ያልተጣራ ፍሳሽ መጋቢት በ2018 እ.ኤ.አ ባጋጠመ ጊዜያዊ አደጋ ካልሆነ በስተቀር ፍሳሽ በጭራሽ ከፓርኩ ወጥቶ እንደማያውቅ፤ ዜሮ ሊክዊድ ዲስቻርጅ (ZLD) ፍሳሽ ማጣሪያ ማለት ፍሳሽን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የማጣራት ዘዴ ሲሆን ማንኛውም ወደ ፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ የገባ ፍሳሽ ከጎጂ ኬሚካሎች ፀድቶ እና የጥራቱም ደረጃ መልሶ ለምርት ለመጠቀም በሚያስችል ሁኔታ ፍሳሽን ማጣራት መቻል መሆኑን፤
- ✓ ይሁንና ከዚህ ጋር በተያያዘ አምራች ድርጅት ምርት በሚቀንስበት አልያም ፕሮሰስ በሚቀይርበት ወይም አረንጓዴ ስፍራ ውሃ በማይፈልግበት ጊዜ ለምርት የሚያስፈልገዉ ዉሃ ከጊዜ ወደ ጊዜ ይለያያል፤ በዚህም ጊዜ ለምርትነት ሊጠቅም የሚችል የተጣራ ዉሃ በማጣሪያዉ ጣቢያ ሲከማች የዉሃ ልዩነት (Imbalance) የሚያመጣ በመሆኑ የተጣራ ፍሳሽ ወደ ውጭ ሊወጣ የሚችልበት እድል መኖሩን፣
- ✓ ፍሳሽ ወደ ሀይቅ ይገባል የሚለውን በቀጥታ ከፓርኩ ጋር ማያያዝ ተገቢነት የሌለው እንዲሁም በተፋሰሱ ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት በሙሉ የፓርኩ ችግሮች እንደሆኑ መደምደም ተገቢ አለመሆኑን፣ በተጨማሪ የዜሮ ፍሳሽ ቴክኖሎጂ Zero Liquid Discharge (ZLD) ፍሳሽ ማጣሪያ መስመር ከጎርፍ ማስወገጃ መስመር ጋር እንዲገናኝ ተደርጎ ያልተገነባ መሆኑን፤
- ✓ በኮርፖሬሽኑ አደረጃጀት በደረጃ አንድ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የአካባቢ ጥበቃ ባለሙያ በቋሚነት መቅጠር የማይቻል በመሆኑ ችግሩን በጊዜያዊነት ለመፍታት የሠዉ ሃይል መመሪያ በሚፈቅደው አግባብ የአካባቢ ጥበቃ ባለሙያዎች በኮንትራት ለመቅጠር ጥረት የተደረገ መሆኑንና አሁን ኮርፖሬሽኑ አዲስ አደረጃጃት በማስጠናት ላይ ስለሚገኝ ከአካባቢ ጥበቃ ጋር በተያያዘ ያጋጠመው የአደረጃጀት ክፍተት ስለሚቀረፍ ባለሙያዎች በቋሚነት የሚቀጠሩ ይሆናል፡

በማለት ገልፀዋል፡፡

46.የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ይህን ይበሉ እንጂ፡-

❖ ሃላፊዎቹ በምላሻቸው ምንም አይነት ፍሳሽ ከፋብሪካዎቹ ወደ አካባቢው የሚለቀቅ እንደሌለ ቢናገሩም በአዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ ስር ለሚገኘው ኪንግደም ኢትዮጵያ ላይነን ፒ.ኤል.ሲ ለተባለው ድርጅት ቆሻሻ ውሃ ወደ ውጭ በመልቀቁ በቀን 10/02/2014 በደብዳቤ ቁ AIPom/10/03/117/14፣ በቀን 24/02/2014 በደብዳቤ ቁ AIPom/12/03/126/14፣ በቀን 24/04/2014 በደብዳቤ ቁ AIPom/04/03/57/14፣ እና በቀን 24/02/2015 በደብዳቤ ቁ AIPom/19/03/215/15፣ ፓርኩ አራት የማስጠንቀቂያ ደብዳቤዎች ለድርጅቱ የፃፈ መሆኑ እንዲሁም ሰንሻይን ኢትዮጵያ ውል ቴክስታይል ፒ.ኤል.ሲ ለተባለው ድርጅት ደግሞ በቀን 24/01/2014 በደብዳቤ ቁ AIPom/05/03/521/14፣ በቀን 24/02/2014 በደብዳቤ ቁ AIPom/23/03/180/14፣ በቀን 02/05/2014 በደብዳቤ ቁ AIPom/64/03/448/14፣ በቀን 21/02/2015 በደብዳቤ ቁ AIPom/18/03/211/15፣ እና በቀን 30/03/2015 በደብዳቤ ቁ AIPom/20/03/302/15 ቆሻሻ ውሃ ወደ አካባቢ በመልቀቁ አምስት ደብዳቤ የፃፈ ቢሆንም ምንም አይነት የእርምት እርምጃ ባለመወሰዱ ይህን ችግር በኦዲቱ የመስክ ጉብኝት ወቅትም ለማየት በመቻሉ እንዲሁም በቦሌ ለሚ ኢ/ፓርክ ስር የሚገኘው ሱፍሌት ብቅል ፋብሪካ የታከመ ፍሳሽ ወደ ውሃ አካላት መልቀቅ የሚያስችል ፍቃድ ከውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ያገኘ ቢሆንም ከመደበኛው የፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ውጪ ፍሳሹን ወደ አካባቢው የሚለቅ በመሆኑ በተጨማሪ ከማጣሪያው መጥፎ ሽታ የሚወጣና ይህንንም ሽታ መቀነስ እየተቻለ መፍትሄ ያላገኘ መሆኑን በቦታው ላይ በመገኘት ለማየት በመቻሉ፤

❖ በተጨማሪም ከሐዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ ቀለም እና መጥፎ ሽታ ያለው ውሃ ለክረምት የጎርፍ ውሃ መሄጃ ተብሎ ከሐዋሳ ሐይቅ ጋር በቀጥታ እንዲገናኝ ተደርጎ በተሰራው የፍሳሽ መውረጃ (ካናል) አማካኝነት ያለማቋረጥ እየፈሰሰ ቀጥታ ወደ ሐይቁ እየገባ መሆኑ በመስክ ምልከታ የታየ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም።

47.በመሆኑም በኢንዱስትሪ ፓርኮቹ የቆሻሻ አስተዳደርና ክትትል ባለመኖሩ ምክንያት በኢንዱስትሪው ውስጥ እያመረቱ ያሉ አንዳንድ ድርጅቶች የቆሻሻ አያያዝ ሥርዓት ባልተከተለ መልኩ ቆሻሻን ወደ ውጭ እንዲለቁ እና አካባቢው ላይ ብክለት በማስከተል ህብረተሰቡንም ለመተንፈሻ አካላት ችግር እና ለሌሎች በሽታዎች ተጋላጭ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**የአካባቢ ደህንነትንና ጥበቃን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር የሚሰሩ መሆናቸውን በተመለከተ፤**

48. ኮርፖሬሽኑ የኢንዱስትሪ ፓርኮች የአካባቢ ደህንነትንና ጥበቃን በተመለከተ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ሊሰራ ይገባል፡፡

49. ለጨርቃጨርቅ እና አልባሳት ኢንዱስትሪ ፓርኮች የተዘጋጀው የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ መመሪያ ገፅ 16 ላይ (Integrated Solid Waste Management Guideline for Textile and Garment Based Clusters of Industrial Parks, In IPDC) ኮርፖሬሽኑ የኢንዱስትሪ ፓርኮች የደረቅ ቆሻሻ መጣያ ቦታን ለማልማት እንዲሁም ምቹ ፤ በቂ እና ተስማሚ ቦታ ለማግኘት ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር እንደሚሰሩ እንዲሁም ከኮርፖሬሽኑ ዋና ዋና ተግባራት መካከል የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር ላይ ከሚሰሩ ልዩ ልዩ ተቋማት ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር መረጃዎችን መለዋወጥ መሆኑን ይገልፃል።

50. ይሁን እንጂ፡-

- ❖ በአዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ ስር በሚገኘው ኪንግደም ኢትዮጵያ ላይነን ፒ.ኤል.ሲ በተባለው ድርጅት እና በኢ/ፓርኩ መሃል ያለው ክፍት ቦታ የቆሻሻ መጣያና የውሃ ፕላስቲክ ጠርሙሶች ማጠራቀሚያ እንዲሁም አረም የበቀለበት በመሆኑ የኢንዱስትሪ ፓርኩን ደህንነትና ገፅታ እያበላሸ መሆኑ፤



ፎቶ ቁጥር 11. በአዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ ስር ያለው ክፍት ቦታ የቆሻሻ መጣያና ቁጥቋጦ በቅሎበት የሚያሳይ

❖ በአዋጅ ቁጥር 886/2007/አንቀጽ 24 መሰረት የአካባቢ ስርዓቶችን፤ ደረጃዎችን፤ የአካባቢ መንከባከቢያ መንገዶችን እና የአካባቢ ጉዳት መቀነሻ ዕቅዶችን በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ለማስፈጸም፤ ለመቆጣጠር፤ ለመጠበቅ እና ተግባራዊ ለማድረግ የሚያግዝ ቢሮ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ እንደሚደራጁ ቢገልጽም ኮርፖሬሽኑ የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር ላይ ከሚሰሩ ተቋማት ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር፤ መረጃዎችንም በመለዋወጥ ቢሮው እንዲደራጅ ያልተደረገ መሆኑ፡

በተደረገው የመስክ ምልከታና ለሚመለከታቸው ባለሙያዎች በቀረበ መጠይቅ ምላሽ ለማወቅ ተችሏል፡፡

51. ስለጉዳዩ የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ፣ እንዲሁም ለኮርፖሬሽኑ በተላከው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ወቅት በሰጡት ምላሽ፡-

✓ ይህ ክፍት ቦታ ኪንግደም ኢትዮጵያ ላይነን ፒ.ኤል.ሲ በሁለተኛ ምዕራፍ ለማልማት ንኡስ ሊዝ የወሰደው ቦታ ሲሆን ለኢንዱስትሪ ፓርኩ በቂ የኤሌክትሪክ ሃይል ሲቀርብለት ግንባታ የሚጀምር መሆኑንና እስከዚያዉ አጥሮ እንዲያስጠብቅ ማሳሳቢያ ተሰጥቶት ክትትልም እንደሚደረግበት፤

✓ ቢሮ ማቋቋምን በተመለከተ ይህንን ጥያቄ መመለስ ያለበት ኃላፊነት ተሰጠው የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን መ/ቤት መሆኑን፡ ይሁንና ኮርፖሬሽናቸው በአዋጅ ቁጥር 886/2007 አንቀጽ 24 መሠረት የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤት ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ቢመጣ ኮርፖሬሽኑ በአንድ መስኮት አገልገግሎት መስጫ ውስጥ ቢሮ ለመስጠት ዝግጁ መሆኑን፡ ለዚህም በተደጋጋሚ ደብዳቤ የተፃፈለት ቢሆንም በአንድ መስኮት አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን ለማስተባበር በኢንዱስትሪ ፓርኮች አዋጅም ሆነ ደንብ የተሰጠዉ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽንም ተደጋጋሚ ማሳሰቢያ ቢሰጥም ተፈጻሚ አለመሆኑን፤

ገልፀዋል፡

52. በተጨማሪም የኢ.ፌ.ድ.ሪ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ህግ ተከባሪነት ክትትልና ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ጀነራል ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፤ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ቢሮ ማቋቋምን በተመለከተ የአደረጃጀት መዋቅር እየሰሩ እንደነበርና በዚህም ምክንያት በኢንዱስትሪ ፓርኮች ባለሙያ ለመመደብ እና ወደ ታች ለመውረድ አደረጃጀቱ ያልፀደቀ በመሆኑ እንደ ክፍተት እንደሚያዩት ገልፀዋል፡፡

53.የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ይህን ይበሉ እንጂ፡-

- ❖ በኪንግደም ኢትዮጵያ ላይነን ፒ.ኤል.ሲ በሁለተኛ ምዕራፍ ለማልማት ንኡስ ሊዝ የወሰደው ቦታ መሆኑ ቢገለፅም በመስክ ጉብኝቱ ወቅት እንደታየው በአጥር ያልተከለለና ምንም አይነት ጅምር የልማት ስራዎች ያልተከናወኑበት እና ቆሻሻ የተጠራቀመበት እንዲሁም አረም የበቀለበት በመሆኑ፣የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

54.በመሆኑም፡-

- ❖ በኪንግደም ኢትዮጵያ ላይነን ፒ.ኤል.ሲ በተባለው ድርጅት እና በኢንዱስትሪ ፓርኩ መሃል ያለው ክፍት ቦታ የቆሻሻ መጣያ እና አረም የበቀለበት በመሆኑ ለአይን እይታ የሚረብሽ መሆኑ እንዲሁም ፤በኢንዱስትሪ ፓርኩ ለሚሰሩ ሰራተኞች የደህንነት ስጋት እና ለፓርኩም ገፅታ መበላሸት ምክንያት ሊሆን ይችላል፤
- ❖ እንዲሁም የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ለኢ.ፌ.ድ.ሪ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤት በቀን ነሐሴ 16/2014 በቁ.ኢ..ፓ/290/75 በኢንዱስትሪ ፓርክ ቅርንጫፍ አንድ ማዕከል ገብተው አገልግሎት እንዲሰጡ ደብዳቤ የፃፈ ቢሆንም የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤት የሚጠበቅበትን ሃላፊነት ባለመወጣቱ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር ላይ የሚሰራ ገለልተኛ ቢሮ እንዲቋቋም ካልተደረገ ፋብሪካዎቹ በምርት ሂደት በአካባቢው ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉትን ብክለት በቅርብ ሆኖ ለመከታተልና ወቅታዊ ማስተካከያ እንዲወስዱ የማድረግ ሂደትን አስቸጋሪ ሊያደርገው ይችላል፡፡

## ኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚጠቀሟቸው ኬሚካሎች አቅርቦት እና መረጃ አያያዝና ሪፖርት በተመለከተ

55.ኮርፖሬሽኑ ኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚጠቀሟቸው ኬሚካሎች መረጃ በየአመቱ ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሪፖርት ሊያደርግ፤ እንዲሁም የኬሚካል አቅርቦት እና ዝቃጭ (Sludge) ማኔጅመንት ውጤታማ ለማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ ሊሰራ ይገባል፡፡

56.የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ምዝገባ አስተዳደር አዋጅ ቁ.1075/2010 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ ኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚጠቀሟቸው ኬሚካሎች መረጃ በየአመቱ ለኢንዱስትሪ ሚ/ር ሊልኩ እንደሚገባ ይገልፃል፡

57.ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

❖ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚገኙ አምራቾች የሚጠቀሙትን የኬሚካል አይነት እና መጠን ለኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የማያሳውቁ እና ኮርፖሬሽኑም ለኢንዱስትሪ ሚ/ር በኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ምዝገባ አስተዳደር አዋጅ ቁ.1075/2010 መሰረት የተጠቀሙትን የኬሚካል አይነት የማያሳውቅ መሆኑ፤

❖ በተጨማሪም ኢንዱስትሪ ፓርኮች ለፍሳሽ ቆሻሻ መጣሪያ የተለያዩ ኬሚካሎች የሚጠቀሙ በመሆኑ ኮርፖሬሽኑን ለከፍተኛ ወጪ እየዳረገ እና ሃገር ውስጥ የማይገኙ ኬሚካሎቹም ከውጭ ሃገር ስለሚገቡ ለፍሳሽ ቆሻሻ ማጣራት ከውጭ ለሚገቡት ኬሚካሎች ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ በኢ/ፓርኮች አዋጅ ቁ.886/2007 ክፍል 2 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 9 እንዲሁም የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁ.300/1995 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት ኮርፖሬሽኑ ለገንዘብ ሚ/ር በደብዳቤ ቁጥር ኢ.ፓልኮ/011/891/011 በ30/12/2014 ዓ.ም ደብዳቤ የፃፈ ቢሆንም፤ ኬሚካሎቹ ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ ዕድሉ እንዲመቻች ያልተደረገ መሆኑን፡

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱት ሰነዶችና ከሚመለከታቸው የኢንዱስትሪ ፓርኮች ኃላፊዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

58.ስለጉዳዩ የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ፣ እንዲሁም ለኮርፖሬሽኑ በተላከው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ወቅት በሰጡት ምላሽ፡-

- ✓ ይህን አዋጅ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በኩል የኬሚካል ምዝገባ ሬጂስትሪ ሲስተም ለማስጀመር የነበረዉ ሂደት ባለመሳካቱ እና ለአዋጁ ማስፈጸሚያ አሰራር መመሪያ ባለመኖሩ ሥራዉን ማከናወን አልተቻለም፡፡ በመሆኑም በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚገኙ አምራቾች የሚጠቀሙትን የኬሚካል አይነት እና መጠን ለኢንዱስትሪ ፓርኩ እንዲያሳውቁ ኢ/ፓርኮቹም ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሪፖርት እንዲያደርጉ ከተፈለገ የሥራዉ ባለቤት የሆነው የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት እንደሚኖርበት፤እና
- ✓ ኮርፖሬሽኑ የኬሚካል ምርቶች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ባቱ ኮስቲክ ሶዳ እና አዋሽ መልካሳ ድረስ በመሄድ ለማጣራት ሂደት የሚሆን ጥራት ያለው ኬሚካሎች እንዲመርቱ ወይይቶች ማድረጋቸውን፡፡ በተጨማሪ ከአዋሽ መልካሳ የአልሙኒየም ሰልፌት እና ሰልፈሪክ አሲድ ፋብሪካ ለፍሳሽ ማጣሪያ የሚሆኑ ኬሚካሎች በዘላቂነት ለመግዛት ጉዳዩ ከሚመለከተው ኬሚካል ኮርፖሬሽን ጋር የመግባቢያ ስምምነት መፈረሙን፡

ገልፀዋል፡፡

59.የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ይህን ይበሉ እንጂ፡-

- ❖ ኮርፖሬሽኑ በአዋጁ መሰረት በውስጡ ያሉት ፋብሪካዎችና ኢንዱስትሪ ፓርኮቹ የሚጠቀሙትን ኬሚካል ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እንዲያውቁት ለማድረግ የአፈፃፀም መመሪያ እንዲሁም በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የኬሚካል አመዘጋገብ ስርዓት አለመፈጠሩ ኮርፖሬሽኑ ያለውን የኬሚካል መረጃ ሪፖርት እንዲያደርግ የማያግድ እና አዋጁ ራሱ በቂ በመሆኑ፤
- ❖ በተጨማሪም ኮርፖሬሽኑ ለፍሳሽ ማጣሪያ የሚሆን ኬሚካል በከፍተኛ መጠን የሚጠቀም እንደመሆኑ መጠን ከውጭና ከአገር ውስጥ አስመጪዎች የሚገዛ በመሆኑ ኮርፖሬሽኑን ለከፍተኛ ወጪ እየዳረገው ይገኛል፡፡

60.በመሆኑም ኢንዱስትሪ ፓርኮቹና በውስጣቸው የሚገኙ ፋብሪካዎች የሚጠቀሙትን ኬሚካልና ንጥረ ነገሮች ለኮርፖሬሽኑ የማያሳውቁ፤ እንዲሁም ኮርፖሬሽኑ ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የማያሳውቅ ከሆነ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴርም በአዋጅ የተሰጠውን ስልጣን ተግባራዊ የማያደርግ ከሆነ በአገሪቱ ውስጥ የኢንዱስትሪን ዘርፍ የኬሚካል አጠቃቀም ከአገር እውቅና ውጪ በመሆን ለማስተዳደርና ለመቆጣጠር የሚያስቸግር እንዲሁም ምቹ አካባቢ መፍጠር ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

በተጨማሪም ኮርፖሬሽኑ ዝቃጩ የሚወገድበትንና ለፍሳሽ ማጣሪያ የሚጠቀምባቸውን ኬሚካሎች ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ ድጋፍ ካልተደረገ፤ ኮርፖሬሽኑን ለተጨማሪ ወጪ በመዳረግ እና የፍሳሽ ማጣራት አቅሙን በማዳከም ያልተጣራ ፍሳሽ ወደ አካባቢው እንዲለቀቅ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

## በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ለሚሰሩ ሰራተኞች ስለ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ የግንዛቤ ማስጨበጫ መሰጠቱን በተመለከተ፡

61.ኮርፖሬሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ለሚሰሩ ሰራተኞች የደረቅ እና ፈሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና እንዲያገኙ ሊያደርግ ይገባል፡፡

62.ይሁን እንጂ በናሙና በታዩት (ቦሌ ለሚ፣ አዳማ፣ ድሬዳዋ፣ ሐዋሳ) ኢንዱስትሪ ፓርኮችም ሆኑ ኮርፖሬሽኑ ከደረቅ እና ፈሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ጋር ተያይዞ ለአምራች ድርጅቶች እና ለፓርኩ ሰራተኞች በቂ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ያልሰራ መሆኑን መጠይቅ ከቀረበላቸው በፓርኮቹ ውስጥ ከሚገኙ አምራች ድርጅቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

63. ስለጉዳዩ የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ፣ እንዲሁም ለኮርፖሬሽኑ በተላከው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ወቅት በሰጡት ምላሽ፡-

- ✓ ኮርፖሬሽኑ የደረቅ እና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ በተመለከተ ከኩባንያዎች ጋር በተደረገ ዉል መሰረት፤ የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ኮርፖሬሽኑ አዉት ሶርስ (outsource) ባደረጋቸዉ ድርጅቶች/ማህበራት አማካኝነት እየተወገደ ሲሆን፤ ተያያዥ በሆኑ የአካባቢ ጉዳዮች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች ለመስጠት ጥረት ያደረገ ቢሆንም ስልጠናዎች በቂ ባለመሆናቸው ወደ ፊት በዚህ ዙሪያ ብዙ መስራት እንዳለብን እናምናለን በማለት ገልፀዋል፡፡

64. የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ይህን ይበሉ እንጂ፡-

- ❖ ስልጠና የተሰጠባቸውን መድረኮች ማስረጃ ያልቀረበና በናሙና ተመርጠው የመስክ ምልከታ የተደረገባቸው በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚገኙ አምራች ድርጅቶች በቀረበላቸው መጠይቅ በደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ዙሪያ ከኢንዱስትሪ ፓርኩ ምንም አይነት ስልጠና እንዳላገኙ ገልፀዋል፡፡

65. በመሆኑም ኮርፖሬሽኑ በደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ዙሪያ ለፓርኩ አምራች ድርጅቶች ስልጠና ባለመስጠቱ፤ በአንዳንድ አምራች ድርጅቶች ውስጥ የቆሻሻ አያያዝ ችግሮች ያለ ሲሆን፤ በአልሚ ድርጅቶች ውስጥ የሚሰሩ ሠራተኞች በቂ ግንዛቤ ማስጨበጫ ካልተሰጣቸው በጤናቸው እና በአካባቢው ላይ የከፋ ችግር ሊያደርስ ይችላል፡፡

## የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ ግንባታ በዲዛይኑ መሰረት በወቅቱ ተጠናቀው ወደ ስራ መግባታቸውን በተመለከተ፡

66. ኮርፖሬሽኑ የኢንዱስትሪ ፓርኮች የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ ግንባታ ስራዎች በዲዛይኑ ውስጥ ተካተው በተያዘው ዕቅድና ውል መሰረት በወቅቱ ተጠናቀው ወደ ስራ ስለመግባታቸው ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

67. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፤ ደብረ ብርሃን እና ባህር ዳር ኢንዱስትሪ ፓርክ የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ ግንባታ ስራዎች በኮርፖሬሽኑ አመታዊ ዕቅድ ማለትም በ2013 ዓ.ም እና በ2014 ዓ.ም 100% ለማጠናቀቅ ዕቅድ የተያዘ ቢሆንም፤ በተያዘው ዕቅድ መሰረት በወቅቱ ተጠናቀው ወደ ስራ ያልገቡ መሆኑ ከቀረበው ሰነድ ክለሳ የታየ ሲሆን፤ የድሬዳዋ ኢንዱስትሪ ፓርክ የፍሳሽ ማጣሪያ ግንባታ ቢጠናቀቅም ወደ ስራ ያልገባ መሆኑ በመስክ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡

68.ስለጉዳዩ የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ፣ እንዲሁም ለኮርፖሬሽኑ በተላከው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ወቅት በሰጡት ምላሽ፡-

- ✓ የደብረ ብርሃን እና ባህርዳር ኢንዱስትሪ ፓርኮች የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ ግንባታ ከኮንትራት አስተዳደር ጋር በተፈጠረ ተግዳሮት ምክንያት ግንባታው በሚፈለገው ፍጥነት እየተከናወነ አይደለም፡፡ድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጠናን በተመለከተ የፍሳሽ ማጣሪያው ቢጠናቀቅም ከፋብሪካ ሼዶች የሚለቀቅ የኢንዱስትሪ ፍሳሽ ባለመኖሩ እስካሁን የፍሳሽ ማጣራት ሥራ ለመጀመር አልተቻለም ብለዋል፡፡

69.በመሆኑም የደብረ ብርሃን እና ባህርዳር ኢንዱስትሪ ፓርኮች የፍሳሽ ማጣሪያ ግንባታዎች በተያዘላቸው ዕቅድ መሰረት እንዲጠናቀቁ ተገቢው ክትትልና ድጋፍ ካልተደረገ ባለሃብቶች በብዛት ወደ ፓርኮቹ እንዳይገቡ፤ ለዜጎች የስራ ዕድል እንዳይፈጠር እና ኮርፖሬሽኑን ለአላስፈላጊ ወጪ ሊዳርግ ፣ በተጨማሪም የተጠናቀቀው የድሬደዋ ኢንዱስትሪ ፓርክ ፍሳሽ ማጣሪያ አገልግሎት እንዲሰጥ ካልተደረገ በወደፊት የማጣራት ሂደቱ ላይ ችግር ሊፈጠር ይችላል፡፡

## የለማ ኢንዱስትሪ ፓርክን ለአምራች ድርጅቶች ያቀረበ/ያስተላለፈ መሆኑን በተመለከተ

70.ኮርፖሬሽኑ የለማ ኢንዱስትሪ ፓርክን ለአምራች ድርጅቶች ሊያቀርብ/ሊያስተላልፍ ይገባል፡፡

71.ይሁን እንጂ፤ በኢንዱስትሪ ፓርኮች አዋጅ 886/2007 አንቀጽ 6/(6) መሰረት ያልለማ ኢንዱስትሪ ፓርክ መሬት ማስተላለፍ የለበትም የሚል ቢሆንም፤ ኮርፖሬሽኑ ያልለማ መሬት ለባለሃብቶች ያስተላለፈ መሆኑን በናሙና የታዩ መጠይቅ የቀረበላቸው (በውሺ ነምበር ዋን ኮተን ኢትዮጵያ ፤ልዩ ሺታኦ ፋክትሪ፤ጆተን ቀለም ፋብሪካ የመሳሰሉት) ድርጅቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

72.ስለጉዳዩ የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ እና በተላከው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ወቅት በሰጡት ምላሽ፡-

- ❖ ጊዜያዊ የደረቅ ቆሻሻ ማቆያ አለመገንባቱ ኮርፖሬሽኑ ያልለማ መሬት አስተላልፏል ለማለት የማያስችልና በኢንቨስትመንት ቦርድ ፈቃድ መሰረት መሬቱን ለአልሚዎች ያስተላለፉ መሆኑን ገልፀዋል፤

73.የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ይህን ይበሉ እንጂ፡-

ኮርፖሬሽኑ ሌሎች መሰረተ ልማቶች ያሟላ ቢሆንም፤ መሬት የተላለፈላቸው አምራቾች የደረቅ ቆሻሻ ማቆያ ስፍራ ያላዘጋጁ በመሆኑ ምክንያት የድርጅቶቹ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ደካማ ሊሆን ችሏል፡፡ ለአብነትም በውሺ ነምበር ዋን ኮተን ኢትዮጵያ ፋብሪካ ውስጥ ተረፈ ምርቱ (ቆሻሻው) በግቢው ውስጥ በየቦታው ተጥሎ የሚታይና ለእይታም የማይመችና የግቢውንም ውበት እያበላሸ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ የኦዲት ቡድኑ ለመቀበል ይቸገራል፤

74.በመሆኑም በኢንዱስትሪ ፓርኮች ያልለማ መሬት ለአምራቾች በመተላለፉ፤በተጠቀሱት ድርጅቶች የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአት ደካማ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

## ለ72 ሰአታት የፍሳሽ ቆሻሻ የሚይዝ የፍሳሽ ማጠራቀሚያ ታንከር መገንባቱን በተመለከተ

75.ኮርፖሬሽኑ የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅቶች የፋብሪካው የዋናው የፍሳሽ ማጠራቀሚያ መስመር ድንገተኛ ብልሽትና ጥገና ሲደረግ ቢያንስ ለ72 ሰአታት ፍሳሽ ቆሻሻ የሚይዝ የቤት ውስጥ እና የኢንዱስትሪ ፍሳሽ ማጠራቀሚያ ታንከር እንዲገነቡ ሊያደርግ ይገባል፡፡

76.ይሁን እንጂ፤ በቦሌ ለሚ፣ አዳማ፣ ድሬዳዋ፣ ሐዋሳ፣ ባህር ዳር፣ ኮምቦልቻ፣ ደ/ብርሃን እና ጅማ ኢንዱስት ፓርኮች ውስጥ ከሚገኙ 64 ፋብሪካዎች መካከል በናሙና ከታዩት በሐዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ አንድ ፋብሪካ (ጄፒ ቴክስታይል) ለ2 ቀናት የሚያቆይ እና በአዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ ሁለት (ኪንግደም እና ሰንሻይን) የተባሉ ፋብሪካዎች ብቻ የፍሳሽ ማጠራቀሚያ ታንከር የገነቡ ሲሆን የተቀሩት ግን በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ማለትም ለ72 ሰዓት ፍሳሽ ቆሻሻ የሚያቆይ ታንከር ያልገነቡ መሆኑ፡ ከተከለሱት ሰነዶች እና ከተለያዩ የኮርፖሬሽኑ የሥራ ኃላፊዎች፣ ከአምራች ድርጅቶች ከተሰበሰቡ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

77.ስለጉዳዩ የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ፣ እንዲሁም ለኮርፖሬሽኑ በተላከው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ወቅት በሰጡት ምላሽ፡-

- ሁሉም የኢንዱስትሪ ፍሳሽ የሚለቁ ባለሀብቶች ለ72 ሰዓት ከኢንዱስትሪያቸው የሚመነጭ ፍሳሽ ማጠራቀም የሚችል ታንከር እንዲገነቡ ተደጋጋሚ ትዕዛዝ የተሰጣቸዉ ሲሆን፤ አንዳንድ ባለሀብቶች የተለያዩ ምክንያቶችን በመደርደር እስካሁን ግንባታ ያልጀመሩ እንዳሉና ነገር ግን ኢንዱስትሪ ፍሳሽ የሚለቁ ባለሀብቶች ጊዜያዊ የፍሳሽ ማጠራቀሚያ ታንከር መገንባት የማይቀር ግዴታቸው ነው ብለዋል፡፡

78.በመሆኑም ፋብሪካዎች የራሳቸውን ፍሳሽ የሚያቆይ ታንከር ካልገነቡ በኢንዱስትሪ ፓርኩ የፍሳሽ ማጣሪያ ላይ ድንገተኛ ብልሽት ቢያጋጥም ፍሳሻቸው ሳይታከም ወደ አካባቢው ሊለቀቅ ይችላል፡፡

## አምራች ድርጅት በጊዜያዊ የማከማቻ ስፍራ አደገኛ ቆሻሻን ከአንድ ወር በላይ የማያከማች መሆኑን በተመለከተ፡

79.ኮርፖሬሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም አምራች ድርጅት በጊዜያዊ የማከማቻ ስፍራ አደገኛ ቆሻሻን ከአንድ ወር በላይ እንዳያከማች ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

80.የአደገኛ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አዋጅ ቁ.1090.አንቀፅ 6/4 ላይ በጊዜያዊ የማከማቻ ስፍራ አደገኛ ቆሻሻን ከአንድ ወር በላይ እንዳይከማች ያዛል።

81.ይሁን እንጂ፡-

- ❖ በናሙና በታዩት ኢንዱስትሪ ፓርኮች አደገኛ ቆሻሻ ናቸው ተብለው የተለዩ ቆሻሻዎች (ፍሎረሰንት መብራት፣ ኬሚካል የመጣባቸው በርሜሎች፣ ጊዜ ያለፈባቸው የፍሳሽ ማጣሪያ ኬሚካሎች (በሃዋሳ ኢ/ፓርክ) እና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻን ጨምሮ) ቢኖሩም ሳይወገዱ ከ6 ዓመታት በላይ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ በመስክ ምልከታ፣ ከተከለሱት ሰነዶች ፣ ከአምራች ድርጅቶች እና ከተሰበሰቡ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡




**ፎቶ ቁጥር 12. በሐዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ ሳይወገዱ ለረዥም ጊዜ ተከማችተው የሚገኙ አደገኛ ቆሻሻዎች በከፊል**




**ፎቶ ቁጥር 13. በሐዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ ሳይወገዱ ለረዥም ጊዜ ተከማችተው የሚገኙ የፍሳሽ ማጣሪያ ኬሚካል በከፊል**

82.ስለጉዳዩ የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ፣ እንዲሁም ለኮርፖሬሽኑ በተላከው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ወቅት በሰጡት ምላሽ፡-

- ✓ አደገኛ ቆሻሻን በአዋጅ ቁጥር 1090/2018 (የአደገኛ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ) መሠረት ለማዘዋወርም እና ለማስወገድ አግባብነት ካለዉ መስሪያ ቤት ፍቃድ ወስዶ የሚሰራ አካል ባለመገኘቱ የተጠቀሱት ቆሻሻዎች ከሌላ ቆሻሻ ዓይነት ተለይተዉ እንዲጠራቀሙ መደረጉን፡ቢሆንም ግን ችግሩ የሚጠይቀዉ ሁሉን አቀፍ መፍትሄ (Comprehensive Solution) በመሆኑ፤
- ✓ ኮርፖሬሽኑ የአደገኛን ቆሻሻ ከምንጩ የማድረቅ መርህን እና አዋጅ ቁጥር 1090/2018 መሠረት ያደረገ የአደገኛ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ መመሪያ በማዘጋጀት በማፀደቅ ሂደት ላይ እንደሚገኝ እና በኢንዱስትሪ ፓርኮች የአደገኛ ቆሻሻ ምንጭ በዋናነት ፍሎረሰንት መብራት (Flourescent Bulb) መሆኑን ይህንም ፍሎረሰንት መብራት (Flourescent Bulb) ምንም ጉዳት በሌለው ኤል.ኢ.ዲ መብራቶች (LED Lights) ለመተካት ከአምራች ድርጅቶች እና አጋር አካላት ጋር እየተሰራ እንደሚገኝ፡

ገልፀዋል፡

83.በመሆኑም አዋጅ ቁጥር 1090/2018ን መሠረት ያደረገ የአደገኛ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ መመሪያ በሚመለከተው አካል እንዲዘጋጅና እንዲፀድቅ ብሎም ተግባራዊ እንዲሆን ካልተደረገ

በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚገኙ አደገኛ ቆሻሻዎች ኢንዱስትሪ ፓርኮቹ ከተቋቋሙ ጀምሮ ያልተወገዱ እና ባለው ሁኔታ ለዓይንም በማይመች ሁኔታ የተቀመጠ በመሆኑ በጊዜ ሂደት ቆሻሻዎቹ ተጠራቅመው ከፓርኮቹ አቅም በላይ በመሆን አደጋ ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡

## ኮርፖሬሽኑ ለአምራች ድርጅቶች የፍሳሽ መለኪያ መሳሪያ እንዲገጠም ማስደረጉን በተመለከተ

84. ኮርፖሬሽኑ የኬሚካል ፍሳሻ ያላቸው በፓርኩ ውስጥ የሚገኙ ድርጅቶችን በመለየት በእያንዳንዳቸው የፍሳሽ መለኪያ መሳሪያ (flow meter) እንዲገጠም ሊያደርግ ይገባል፡፡
85. ይሁን እንጂ፡- ኮርፖሬሽኑ የኬሚካል ፍሳሽ ያላቸው በውስጡ የሚገኙ ድርጅቶችን በመለየት ለእያንዳንዳቸው የፍሳሽ መለኪያ መሳሪያ (flow meter) ያስገጠመ ቢሆንም፤ በቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ የሚገኘው አሸተን አፓረል ማኑፋክቸሪነግ ውስጥ የተገጠሙት (flow meter) ብልሽት ያጋጠማቸው እና ለረጅም ጊዜ የማይሰሩ መሆኑ ለአምራች ፋብሪካዎች ከቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ እና በመስክ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡
86. ስለጉዳዩ የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ እና ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ፡-

   ✓ ፍሎው ሜትሮች በፍሳሽ ማጣራት ሂደት ዉስጥ ያላቸው ሚና ከፍተኛ ሲሆን፤ ድርጅቶችም ወደ ስራ ሲገቡ እንዲገጠሙ ከማድረግ ጀምሮ መሳሪያዎቹ ብልሽት እንዳያጋጥማቸዉ እንክብካቤ እና ጥገና ማድረግ ያስፈልጋል ፤ ምክንያቱም ፍሎ ሜትሮቹ ሀገር ውስጥ ስለማይገኙ በውጭ ምንዛሬ ከውጭ ተገዝተው የሚመጡ በመሆኑ፤ የተበላሹ ፍሎ ሜትሮች በማዕከል ለመግዛት አለም አቀፍ ጨረታ ወጥቶ በሂደት ላይ የሚገኝ ሲሆን፤ ግዥው ተከናውኖ ፍሎ ሜትሮቹ እስኪተከሉ ድረስ በአለም አቀፍ ተሞክሮ ታሳቢ በማድረግ የፍሳሽ ማጣሪያ አገልግሎት ክፍያ በሚገባው ውሃ መጠንና በምርት ሂደት ሊባክን የሚችል ውሃ በማስላት (assumption of water loss percentage during production processes) ተግባራዊ እየተደረገ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

87. በመሆኑም የፍሳሽ መለኪያ መሳሪያ (flow meter) ብልሽት ሲያጋጥማቸው አፋጣኝ መፍትሄ ካልተፈለገላቸው ተገቢው የፍሳሽ ማጣሪያ ክፍያ እንዳይሰበሰብ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**በኢንዱስትሪ ፓርኮች አምራች ድርጅቶች የሚለቁትን ፍሳሽ መጠንና ይዘትን መሰረት ያደረገ ክፍያ ስርዓት በተመለከተ**

88. ኮርፖሬሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚገኙ አምራቾች የሚለቁትን ፍሳሽ የኬሚካል መጠን እና ይዘት ታሳቢ በማድረግ ሊለካ ይገባል፡

89. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡- በኢንዱስትሪ ፓርኮች የፍሳሽ ማጣሪያ ክፍያ ታሳቢ የሚደረገው ከአምራች ድርጅቶች የሚለቀቅ የፍሳሽ መጠን ላይ ብቻ የተመሰረተ እና የኬሚካል ይዘት/ ሎድን ታሳቢ ያላደረገ መሆኑ ከተከለሰ ሰነድ እና መጠይቅ ከቀረበላቸው ኢንዱስትሪ ፓርኮች ለማወቅ ተችሏል፡

90. ስለጉዳዩ የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ እና እንዲሁም ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ፡-

- ✓ የፍሳሽ ማጣሪያ ታሪፍ ክፍያ የፍሳሽ መጠንን (Volume Based) የተደረገበት ዋናዉ ምክንያት ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት ቢሆንም፤ የፍሳሽ መጠን (Volume Based) ታሪፍ ግን ገደብ ያለዉ ነው፡፡ ይኸውም የሚለቀቀው ፍሳሽ ለማጣሪያው ከተቀመጠው የገቢ መለኪያ ገደብ (Inlet parameters limit) በላይ የሆነ የኬሚካል ሎድ በተለቀቀው ሎድ መሰረት የቅጣት ክፍያ የሚፈጸም ሲሆን፤ የኬሚካል ሎዱ በጣም የተጋነነ ከሆነ ደግሞ ባለሃብቱ ቅድመ-ማጣራት (Pre-treatment) ማጣሪያ እንዲገነባ እና የፍሳሹ የጥራት ደረጃ ከገቢ መለኪያ ገደብ በታች እንዲሆን ይደረጋል በማለት ገልፀዋል፡፡

91. የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ይህን ይበሉ እንጂ፡-
የፍሳሽ ማጣሪያ ታሪፍ ክፍያ የኦዲት ቡድኑ ለመስክ ምልከታ በፓርኩቹ ተገኝቶ ጉብኝት እስካደረገበት ጊዜ ድረስ የፍሳሽ መጠንን ብቻ መሰረት ያደረገ ሲሆን ከጥር ወር 2015 ዓ.ም ጀምሮ ግን የታሪፍ ማሻሻያ ጥናት አስጠንተው ወደ ተግባር ለመለወጥ እና ባለሃብቶችም ይህንን እንዲያውቁት የማድረግ ጅምር ስራዎች መኖራቸውን ለማየት ተችሏል፡፡

92. በመሆኑም ኢንዱስትሪ ፓርኮች የፍሳሽ ማጣሪያ ክፍያ የኬሚካል ይዘት ታሳቢ በማድረግ የማይለኩ ከሆነ እና በሚያመነጩት ፍሳሽ መጠን ብቻ ክፍያ የሚያስከፍሉ ከሆነ አካባቢው ላይ ከፍተኛ ችግር የሚያደርሱት ተቋማት ከድርጊታቸው እንዳይቆጠቡ እንዲሁም አካባቢ ላይ ጉዳት የማያደርሱት አምራቾች እንዳይበረታቱ ስለሚያደርግ አካባቢን የሚበክሉት ላይ የበለጠ አለማስከፈሉ አካባቢ ላይ ምንም ተጽዕኖ እያደረሱ እንዳልሆነ እንዲያስቡ እና ለአካባቢ ብክለት እንዳይጨነቁ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**አምራቾች ከሚለቁት ፍሳሽ የሚሰበሰብ ገቢ ተመጣጣኝና ወቅታዊ ማስተካከያ የሚደረግበት መሆኑን በተመለከተ፥**

93. ኮርፖሬሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚገኙ አምራቾች ድርጅቶች ከሚለቁት ፍሳሽ የሚሰበሰብ ገቢ ተመጣጣኝና የፍሳሽ ቆሻሻን ለማከም የሚያስችል ወጪን ያገናዘበ፣ ወቅታዊ ማስተካከያ የሚደረግበት እንዲሆንና ለዚሁ አላማ እንዲውል ሊያደርግ ይገባል፡፡

94. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ❖ ኮርፖሬሽኑ ለፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ ያወጣው ወጪ ከባለሃብቶች ለፍሳሽ ማከሚያ ከሰበሰበው ገቢ ጋር ሲነፃፀር ለፍሳሽ መጣሪያ ከፍተኛ ወጪ እያወጣ መሆኑ፣ ለማሳያ- ከ2012ዓ.ም እስከ 2014 ዓ.ም ድረስ ብቻ ብር 404,932,948.88 ወጪ ያደረገ ሲሆን ከባለሃብት የሰበሰበው ገቢ ግን በብር 1,820,674.33 እንዲሁም በዶላር 2,812,672.12 ብቻ በመሆኑ ኮርፖሬሽኑ ከፍተኛ ወጪ እያወጣ እንደሆነ ያሳያል፡፡
- ❖ በኢንዱስትሪ ፓርኮች በሚገኙ አምራች ድርጅቶች ለሚለቀቅ ፍሳሽ በፓርኮቹ የሚሰበሰብ የፍሳሽ ማጣሪያ ገቢ ስርዓት ከሰባት ዓመት በፊት በነበረው የፍሳሽ ቆሻሻን ለማከም የሚያስችል ወጪን ግምት ውስጥ በማስገባት የነበረ ቢሆንም፣ እስከ አሁን ድረስ ያልተሻሻለና የፍሳሽ ቆሻሻ ለማከም ከሚያስችለው ወጪ ያነሰ መሆኑ፣
- ❖ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ለሚገኙ አምራቾች በምርት ሂደት አካባቢ ላይ ለሚያደርሱት ተፅዕኖ ማካካሻ (የአካባቢ መልሶ ማገገሚያ) የአካባቢ የብክለት ለመከላከል የሚያስችል ክፍያ ስርአት ኮርፖሬሽኑ ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር ያልተዘጋጀ መሆኑ፥

በሰነድ ክለሳ እና ለኢንዱስትሪ ፓርኮች ከቀረበ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

95. ስለጉዳዩ የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ፣ እንዲሁም ለኮርፖሬሽኑ በተላከው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ወቅት በሰጡት ምላሽ፡-

- ✓ ኮርፖሬሽኑ የፍሳሽ ቆሻሻ የማከም ታሪፍ ማሻሻያ ጥናት ያደረገ ቢሆንም ከCOVID-19 ወረርሽኝ እና አገራችን ከአጎዋ እድል በመሰረዝ ጋር በተያያዘ ኢንቨስትመንቱ ላይ ጫና በመፈጠሩ ምክንያት ታሪፉን ተግባራዊ ማድረግ አልተቻለም፡፡ ይሁንና አሁን ላይ ለሃዋሳ እና አዳማ ኢንዱስትሪ ፓርኮች የተጠናዉን የፍሳሽ የማከም ታሪፍ ማሻሻያ ጥናት ላይ ከአምራች ድርጅቶች ጋር በመነጋገር በ2023 ተግባራዊ ለማድረግ ዕቅድ መያዙን፤

- ✓ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ 300/2002 መሠረት አምራች ድርጅቶች ለሚያደርሱት ወይም ሊያደርሱ የሚችሉትን ተጽዕኖ በተገቢዉ ደረጃ የመቆጣጠር እና አካባቢን ከብክለት የመጠበቅ ሃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡ በዚሁ መሠረት በምርት ሂደት በአካባቢ ላይ ለሚደርስ ጉዳት (ተፅዕኖ) ማካካሻ (የአካባቢ መልሶ ማገገሚያ) ክፍያ ስርዓት የሚዘረጋው በባለሥልጣን መ/ቤቱ ስለሆነ ሥርዓቱ ሲዘረጋ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ተፈፃሚ ይሆናል፡

በማለት ገልፀዋል፡፡

96. በመሆኑም ኮርፖሬሽኑ ከፍሳሽ ማጣራት የሚሰበስበው ገቢ ፍሳሹን ለማጣራት ከሚያወጣው ወጪ ጋር ባለመጣጣሙ ከፍተኛ ወጪ እንዲያወጣ አድርጎታል፡ ስለሆነም የተዘጋጀውና አምራቾች እንዲያውቁት የተደረገው የማሻሻያ ታሪፍ በተያዘለት መርሃ ግብር ማለትም ከጥር 1/2015 ጀምሮ ተግባራዊ የማይደረግ ከሆነ በወደፊት የኮርፖሬሽኑ የፍሳሽ ማጣራት ሂደት አቅም እንዲያንሰው፤ መንግስትም አካባቢን የሚበክሉ አካላትን በተዘዋዋሪ እየደጎመ እንዲቀጥል እና ያልተጣራ ፍሳሽ ወደ አካባቢው እንዲለቀቅ ምክንያት ሊሆን እና የአካባቢ መልሶ ማገገሚያ ስርአት ከሚመለከተው አካል ጋር በመነጋገር ስርአቱ ካልተዘረጋም ከአምራቾች ጋር በተያያዘ ምክንያት አካባቢ ላይ የሚደርስ ጉዳትን ለመቀነስ የሚደረገውን ጥረትም ሊያዳክም ይችላል፡፡

ከላይ በተመለከቱት የኦዲት ግኝቶች በመነሳት በኢንዱስትሪ ፓርኮቹ የቆሻሻ አያያዝ ሲገመገም በታዩ ግድፈቶች ላይ የተደረሰበቸው የመደምደሚያ ሃሳቦች ቀጥሎ በክፍል ሶሰት ቀርቧል፡፡

# ክፍል ሶስት

***መደምደሚያ***

97. ከላይ በኦዲት ግኝቶች ላይ እንደተመለከተው በኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የኢንዱስትሪ ፓርኮች የተቀናጀ የደረቅ እና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአት አተገባበር ውጤታማ መሆኑ ሲገመገም በታዩ ግድፈቶች ላይ የሚከተሉት የመደምደሚያ ሃሳቦች ተደርሷል፡፡

- ኢንዱስትሪ ፓርኮች ሲቋቋሙ የተጠናላቸው የአካባቢያዊ እና የማህበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት ማዕከላዊ በሆነ መልኩ ለቴክስታይልና ጋርመንት ዘርፍ የተጠና ቢሆንም፤ ከጥናቱ ውጪ ያሉ ዘርፎች በኢንዱስትሪ ፓርኮቹ ውስጥ ገብተው የማምረት ስራ የጀመሩ አሉ፡፡

  በተጨማሪም ኮርፖሬሽኑ በአዲስ አበባ ፣አዳማ ፣ድሬዳዋ እና ሐዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ለሚገኙ 46 ፋብሪካዎች የአካባቢና ማህበራዊ አስተዳደር ዕቅድ እንዲያዘጋጁ በደብዳቤ ያሳወቀ ቢሆንም 37ቱ ፋብሪካዎች ግን ይህን ዕቅድ አዘጋጅተው በሚመለከተው አካል አላፀደቁም፡፡
- በኢንዱስትሪ ፓርኮች ከፍሳሽ ማጣሪያ የወጣው ዝቃጭ (በተለይ በሐዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ) ለዝናብ በተጋለጠ ሁኔታ ከ5 ዓመታት በላይ በፓርኩ ግቢ ውስጥ ተከማችቶ (በከፊል ሼድ ውስጥ፤ በኮንቴነር፤ በአሮጌ የማደበሪያ ጆንያዎች ተደርጎ በተለያዩ ቦታዎች) በወቅቱ በአግባቡ እንዲወገድ አልተደረገም።
- ከአንዳንድ ኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚለቀቀው ፍሳሽ (ከሐዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ ቀለም እና መጥፎ ሽታ ያለው ውሃ ለክረምት የጎርፍ ውሃ መሄጃ ተብሎ በተዘጋጀው የፍሳሽ ማስወገጃ (ካናል) እየፈሰሰ ቀጥታ ወደ ሐዋሳ ሐይቅ የሚገበው፤ በአዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ-ከኪንግደም ኢትዮጵያ ላይነን ፒ.ኤል.ሲ እና ሰንሻይን ኢትዮጵያ ውል ቴክስታይል ፒ.ኤል.ሲ እና በቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ - ሱፍሌት ብቅል ፋብሪካ የፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ውጪ ፍሳሹ ወደ ማሳ (እርሻ) የሚገባ እና ከማጣሪያውም መጥፎ ሽታ የሚወጣ በመሆኑ) ወደ አካባቢ የሚለቁ መሆናቸው አካባቢውን ለብክለት አጋልጧል፡፡
- በሀዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ ለዝቃጭ ማድረቂያ ከፍተኛ ማሽነሪ ከፍሳሽ ማጣሪያው ጋር የተቋቋመ ቢኖርም፤ ማሽነሪው መስራት እየቻለ ዝቃጭ የማድረቁ ሂደት በጸሐይ ኃይል እንዲሆን እና ለማድረቂያ የተዘጋጀ ቦታም ሳይኖር በግቢው የመተላለፊያ መንገድ ላይ

ተበትኖ በጸሐይ ኃይል እንዲደርቅ ሲደረግ በንፋስ ኃይል እየተበተነ የአካባቢ ብክለት እያስከተለ ይገኛል፤

- ኢንዱስትሪ ፓርኮች ከፍሳሽ ቆሻሻ ማከሚያዎች የሚመነጭን ዝቃጭ ቆሻሻ (Sludge) አካባቢያዊና ማህበራዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ ለማስወገድ የሚሆን ቦታ (የሳኒተሪ ላንድ ፊል) በዲዛይናቸው ውስጥ በማካተት እና ቦታውን በማዘጋጀት አገልግሎት እንዲሰጥ ያልተደረገ መሆኑ፤ እና ዝቃጩን ረጂ በመላክ ይወገድ የነበረውም በመቋረጡ በየዓመቱ የሚያዘው ዕቅድ እንዳይተገበር ሆኗል፡፡
- በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚገኙ ድርጅቶች ለምሳሌ(ኪንግደም ኢትዮጵያ ላይነን ፒ.ኤል.ሲ፤ኢንዶቹይን አፓረል፤ፒ.ኤል.ሲ የመሳሰሉት) መረጃ ለመስጠትና ፋብሪካቸውን ለኦዲት ስራ ክፍት ለማድረግ ፈቃደኛ አለመሆናቸው እና የአካባቢ ጥበቃ አካላትም ወደ ፋብሪካዎቹ ገብተው ክትትል ስለማያደርጉ የአካባቢ አያያዛቸው ምን ደረጃ ላይ እንዳለ ለማወቅ አልተቻለም፡፡
- በሐዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ ያሉት የተወሰኑ አረንጓዴ ስፍራዎች የቆሻሻ መጣያ እና የደረቀው ዝቃጭ (ቆሻሻ) እንደማዳበሪያ ተበትኖባቸዋል፡፡
- በድሬዳዋ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውሺ ነምበር ዋን ኮተን ኢትዮጵያ ቴክስታይል የተባለው ድርጅት ግቢ ውስጥ ተረፈ ምርት (ቆሻሻ) ተከማችቶ የሚገኝና እና ከፋብሪካውም በሚወጣ ብናኝ የግቢው ውበት እየተበላሸ ይገኛል፤
- በአዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ ስር በሚገኘው ኪንግደም ኢትዮጵያ ላይነን ፒ.ኤል.ሲ በተባለው ድርጅት እና በኢንዱስትሪ ፓርኩ መሃል ያለው ክፍት ቦታ የቆሻሻ መጣያና የውሃ ፕላስቲክ ጠርሙሶች ማጠራቀሚያ እንዲሁም አረም የበቀለበት በመሆኑ የአካባቢውን ገፅታ አበላሽቷል፡፤
- በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚገኙ አምራቾች የሚጠቀሙትን የኬሚካል አይነት እና መጠን ለኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የማያሳውቁ እና ኮርፖሬሽኑም ለኢንዱስትሪ ሚ/ር በኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ምዝገባ አስተዳደር አዋጅ ቁ.1075/2010 መሰረት የተጠቀሙትን የኬሚካል አይነት አላሳወቁም፤
- ኮርፖሬሽኑ ከደረቅ እና ፈሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ጋር ተያይዞ ለአምራች ድርጅቶች እና ለፓርኩ ነዋሪዎች በቂ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች አልተሰራም፤

- የደብረ ብርሃን እና ባህር ዳር ኢንዱስትሪ ፓርኮች የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ ግንባታ ስራዎች በኮርፖሬሽኑ አመታዊ ዕቅድ ማለትም ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ 100%

ለማጠናቀቅ ዕቅድ የተያዘ ቢሆንም በዕቅዱ መሰረት አልተጠናቀቀም፤ እንዲሁም የድሬዳዋ ኢንዱስትሪ ፓርክ የፍሳሽ ማጣሪያ ግንባታ ቢጠናቀቅም ወደ ስራ አልገባም፤

- ኮርፖሬሽኑ ለባለሃብቶች (ለውሺ ነምበር ዋን ኮተን ኢትዮጵያ ፤ልዩ ሺታኦ ፋክትሪ፤ጆተን ቀለም ፋብሪካ የመሳሰሉት) መሬት ያስተላለፈ ቢሆንም አምራቾቹ የደረቅ ቆሻሻ ማቆያ ስፍራ ያላዘጋጁ በመሆኑ ምክንያት የደረቅ ቆሻሻ አያያዛቸው ደካማ ሊሆን ችሏል፡፡
- በቦሌ ለሚ፣ አዳማ፣ ድሬዳዋ፣ ሐዋሳ፣ ባህር ዳር፣ ኮምቦልቻ፣ ደ/ብርሃን እና ጅማ ኢንዱስት ፓርኮች ውስጥ ከሚገኙ 64 ፋብሪካዎች መካከል ሶስት ፋብሪካዎች ብቻ ጊዜያዊ የፍሳሽ ማጠራቀሚያ ታንከር የገነቡ ሲሆን የተቀሩት ግን በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት አልገነቡም ፤
- በኢንዱስትሪ ፓርኮች አደገኛ ቆሻሻዎች (ፍሎረሰንት መብራት፣ ኬሚካል የመጣባቸው በርሜሎች፣ ጊዜ ያለፈባቸው የፍሳሽ ማጣሪያ ኬሚካሎች፣ እንዲሁም ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻን ጨምሮ) ሳይወገዱ ለረጅም ጊዜ ተከማችተው ተገኝቷል፤
- በቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ የሚገኘው አሽተን አፓረል ማኑፋክቸሪነግ ውስጥ የተገጠሙት (flow meter) ብልሽት ያጋጠማቸው እና ለረጅም ጊዜ የማይሰሩ ተገኝተዋል፤
- በኢንዱስትሪ ፓርኮች የፍሳሽ ማጣሪያ ክፍያ ታሳቢ የሚደረገው ከአምራች ድርጅቶች የሚለቀቅ የፍሳሽ መጠን ላይ ብቻ የተመሰረተ እና የኬሚካል ይዘትን ታሳቢ ያላደረገና የፍሳሽ ቆሻሻን ለማከም የሚወጣውን ወጪ የማይሸፍን ነው፤

98. ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋፅኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አራት አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

99.በኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የኢንዱስትሪ ፓርኮች የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ውጤታማ ለማድረግ ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን የማሻሻያ ሃሳቦች አቅርበናል፡፡

- ኮርፖሬሽኑ ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚገቡ ባለሃብቶች የአካባቢያዊ እና የማህበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት ስራ ከመጀመራቸው በፊት አስጠንተው እንዲገቡና የአካባቢና ማህበራዊ አስተዳደር ዕቅድ እንዲያዘጋጁ እንዲተገብሩ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ከፍሳሽ ማጣሪያ የሚወጣ ዝቃጭ በየጊዜው አካባቢያዊና ማህበራዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ የሚወገድበትን ወይም በጥናት ጥቅም ላይ የሚውልበትን ስርአት ሊዘረጋና ለዝቃጩም ተገቢውን የማቆያ ስፍራ ሊያዘጋጅና ዝቃጭ የማድረቅ ሂደቱም በአካባቢ ላይ ብክለት በማያስከትል መልኩ ለዚሁ በተዘጋጀ የማድረቂያ/ማሽን/ ወይም ስፍራ እንዲደርቅ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚገኙ ፋብሪካዎች Zero Liquid Discharge (ZLD) የሚጠቀሙ በመሆናቸው ምንም አይነት ፍሳሽ እና መጥፎ ጠረን ወደ አካባቢው እንዳይለቁ ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ በሐዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ ያሉት አረንጓዴ ስፍራዎች ተገቢው እንክብካቤ እንዲደረግላቸው እና የቆሻሻ መጣያ እንዳይሆኑ፤ እንዲሁም የደረቀው ዝቃጭ (ቆሻሻ) የአትክልት ስፍራዎቹ ላይ ከመበተኑ በፊት በጥናት ለተክሎቹ ጠቃሚ እና አካባቢን የማይበክል መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚገኙ ባለሃብቶች ለሚመለከታቸውና ህጋዊ አካላት መረጃ መስጠትና ፋብሪካቸውን ለኦዲት ስራ ክፍት ማድረግ እንዲችሉ ጠንካራ ቁጥጥር በማድረግ ግንዛቤ እንዲያገኙ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ በድሬዳዋ ኢንዱስትሪ ፓርክ ስር የሚገኘው ውሺ ነምበር ዋን ኮተን ኢትዮጵያ ቴክስታይል የተባለው ድርጅት ግቢ ውስጥ ያለው ተረፈ ምርት (ቆሻሻ) የሚወገድበትን መንገድ ሊፈልግ እና ብናኙም ከፋብሪካው እንዳይወጣ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ በአዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ ስር በሚገኘው ኪንግደም ኢትዮጵያ ላይነን ፒ.ኤል.ሲ በተባለው ድርጅት እና በኢንዱስትሪ ፓርኩ መሃል ያለው ክፍት ቦታ

የቆሻሻ መጣያና የኢንዱስትሪ ፓርኩ የደህንነት ስጋት እንዳይሆን በአጥር እንዲከለልና የሚለማበትም ሁኔታ እንዲፈጠር ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ኮርፖሬሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የአካባቢ ጥበቃ ቢሮ እንዲቋቋም የጀመረውን ጥረት አጠናክሮ እንዲቀጥልና የኢ.ፌ.ድ.ሪ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤትም በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ቢሮ በማቋቋምና ባለሙያ በመመደብ የቁጥጥር ሃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚገኙ አምራቾች የሚጠቀሙትን የኬሚካል አይነት እና መጠን እንዲያሳውቁት እና ኮርፖሬሽኑም በየወቅቱ ለኢንዱስትሪ ሚ/ር የተጠቀሙትን የኬሚካል አይነት ሪፖርት ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ ከደረቅ እና ፈሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ጋር ተያይዞ ለአምራች ድርጅቶች እና ለፓርኩ ነዋሪዎች በቂ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ሊሰራ ይገባል፤
- ኮርፖሬሽኑ የደብረ ብርሃን እና ባህር ዳር ኢንዱስትሪ ፓርኮች የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ ግንባታ ስራዎች በአፋጣኝ የሚጠናቀቁበትን ዘዴ ሊፈልግና፤ የተጠናቀቀውም የድሬዳዋ ኢንዱስትሪ ፓርክ የፍሳሽ ማጣሪያ ስራ እንዲጀምር ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ ራሱ ገንብቶ ያከራያቸው ሼዶችን የደረቅ ቆሻሻ ማቆያ ስፍራ አሟልቶ ለሁሉም አምራች ድርጅቶች ሊያከራይ/ሊያስተላልፍ እንዲሁም ራሳቸው ገንብተው የሚገቡ ባለሃብቶችም የደረቅ ቆሻሻ ማቆያ ስፍራ ያዘጋጁ መሆኑን ሊከታተል ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚገኙ የኢንዱስትሪ ፍሳሽ ያላቸው ፋብሪካዎች ጊዜያዊ የፍሳሽ ማጠራቀሚያ ታንከር በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት እንዲገነቡ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚገኙ አደገኛ ቆሻሻዎች (ፍሎረሰንት መብራት፣ ኬሚካል የመጣባቸው በርሜሎች፣ ጊዜ ያለፈባቸው የፍሳሽ ማጣሪያ ኬሚካሎች እንዲሁም ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻን ጨምሮ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር የሚወገዱበትን መንገድ ሊፈልግ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ ብልሽት ያጋጠማቸው በፋብሪካዎች ውስጥ የተገጠሙት የፍሳሽ መለኪያ ቆጣሪዎች (flow meter) በአፋጣኝ ተጠግነው ወይም በአዲስ ተተክተው አገልግሎት እንዲሰጡ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች የፍሳሽ ማጣሪያ ክፍያ ከአምራች ድርጅቶች የሚለቀቅ የፍሳሽ መጠን ላይ ብቻ የተመሰረተ ሳይሆን የኬሚካል ይዘት ታሳቢ ያደረገ

እንዲሆን እና ኮርፖሬሽኑ ፍሳሽ ቆሻሻን ለማጣራት በሚያወጣው ወጪ አንፃር በመገምገም በየወቅቱ ክፍያውን ሊያሻሽል ይገባል፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት የኮርፖሬሽኑና የኢንዱስትሪ ፓረኮች የበላይ ሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች፤ እንዲሁም መረጃ የሰበሰብንባቸው የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የስራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ለኦዲቱ ሥራ መሳካት ላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

## አባሪ 1፡ የአካባቢና ማህበራዊ ጉዳዮች መምሪያ ዝርዝር ተግባራት

- የአካባቢና ማህበራዊ የተፅዕኖ ግምገማ እና የመልሶ ማስፈር ዕቅድ የጥናት ሰነዶች የይሁንታ ፈቃድ እንዲያገኙ ማድረግ እና ሁሉም ኢንዱስትሪ ፓርኮች የአካባቢና የማህበራዊ አያያዝ ዕቅድ አዘጋጅተው ተግባራዊ እንዲያደርጉ የሙያ ድጋፍ ያደርጋል፡፡
- የኢንዱስትሪ ፍሳሽና ዝቃጭ እና መርዛማ ኬሚካሎች በፓርኩ እና ከፓርኩ ውጪ በሚገኝ የማህበረሰብ ክፍል ላይ ጉዳት ከማድረሳቸው በፊት አማራጭ የቅድመ-ጥንቃቄ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያስተባብራል
- የመጠጥ ውሃ ማጣሪያ ቴክኖሎጂ ግንባታ እና ኦፐሬሽን ላይ የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤ለፓርኮች የሚቀርብ የመጠጥ ውሃ የሃገር ውስጥና የአለምአቀፍ የጤና ድርጅት የጥራት ደረጃ እንዲያሟላ እና የጥራት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንዲገኝ ያደርጋል፡፡
- በኢንዱስትሪ ፓርኮቹ አግባብ ያላቸው የአካባቢ ደህንነት ጉዳዮች የሚመለከታቸው የፌደራል አስፈፃሚ አካላት ያስቀመጧቸውን ፖሊሲዎች፤ደረጃዎችና አሰራሮች የተከተሉና ያሟሉ መሆኑን ያረጋግጣል፤፤
- የኢንዱስትሪ ፓርኮች የአካባቢና ማህበራዊ ደህንነት ያረጋገጡ እንዲሆኑ የአካባቢና ማህበራዊ ጉዳዮች አሀድ እንዲቋቋም ያስተባብራል፤አግባብ ካላቸው ተቋማት ጋር በመመካከር የፓርኮቹ የአካባቢ ደህንነት ጥበቃ መመሪያ ያዘጋጃል ተግባራ እንዲደረጉ ያስተላልፋል፤ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤ያረጋግጣል፤
- የፓርኮቹ የአካባቢና ማህበራዊ ዕቅድ ትግበራ ላይ ግምገማ ያካሂዳል፤ዘገባ ያቀርባል፤ተቀባይነት ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፤ደረጃቸውን ባልጠበቁ አሰራሮች ላይ የማስተካከያ (ማሻሻያ) እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል፤
- ከፍሳሽ ማጣሪያ የሚመነጭ የኢንዱስትሪ እና ማዘጋጃቤታዊ ስለጅ ለተለያዩ አገልግሎቶች ማለትም ለሃይል ማመንጫ፤ለተፈጥሮ ማዳበሪያነት፤ለወለል ንጣፍ እና ለሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች እንዲውል ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ተቀናጅቶ በመስራት ምርጥ ተሞክሮዎችን እንዲተገበሩ ያደርጋል፤

- የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር ላይ ከሚሰሩ ልዩ ልዩ ተቋማት ጋር የቅርብ ግንኙነት ይፈጥራል፤ መረጃዎችን ይለዋወጣል፤ አለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የብክለት ቁጥጥር መደረጉን ይከታተላል፤ያረጋግጣል፡፡
- የኢኮ-ኢንዱስትሪያል ፓርክ ፍሬም ወርክ እና ፐርፎርማንስ በመላክ እንዲዘጋጅ እና ተግባራዊ እንዲደረግ ያደርጋል፡፡
- አደገኛና በካይ ነገሮችን ለመከላከል የሌሎች አገሮች ተሞክሮዎችን በመውሰድና ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ከአካባቢ ብክለት ነፃ የሆነ አሰራር እንዲተገበር ያበረታታል፤ይከታተላል፤
- ደረጃውን የጠበቀ የአረንጓዴ ልማት ተግባር በየፓርኮቹ ውስጥ እንዲከናወን አቅጣጫ ይሰጣል፤ያስተባብራል፤
- የኮርፖሬት ማህበራዊ ሃላፊነት ስራዎች መከታተልና የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ፤
- የልማት ተነሺዎች የስራ ዕድል እንዲያገኙ ለማድረግ የልማት ተነሺዎች መልሶ ማስፈርና የማቋቋም ስራዎች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካለት ጋር ተቀናጅቶ ይሰራል፤

የሚሉት ናቸው፡፡

## አባሪ 2፡ የኢንዱስትሪ ፓርኮች የደረቅ እና የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ የአሰራር ሥርዓት


- በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ለባለሃብቶች ከሚሰጡ አገልግሎቶች መካከል አንዱ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገድ ሲሆን ከባለሀብቶች የማምረቻ ቦታዎች (ሽዶች) የሚመነጭ ደረቅ ቆሻሻ የሚወገደው ደረቅ ቆሻሻን በሚያነሱ ማህበራት አማካይነት ነው፡፡በመሆኑም ባለሀብቶች ከማምረቻ ሽዶቻቸው የሚመነጭውን ደረቅ ቆሻሻ መልሶ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለውን እና የማይውለውን በመለየት ያጠራቅማሉ፡፡
- በዚሁ መሠረት የደረቅ ቆሻሻ አንሺ መኪኖች ጥቅም ላይ የማይውለውን ቆሻሻ ከየማምረቻ ሽዶች በማንሳት የከተማው ደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ወስደው ይጥላሉ፡፡ይሁንና ከአገልግሎት አከፋፈል ጋር በተያያዘ አንድ አይነት ወይም ወጥ አሰራር የለም እንደ የፓርኮቹ ነባራዊ ሁኔታ ይለያያል፡፡ እንደማሳያ
- ለምሳሌ፡- በቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ቆሻሻ እንዲያነሱ ለተመደቡ ሁለት ማህበራት ቆሻሻ ላነሱበት የአገልግሎት ክፍያ የሚከፍለው በአዲስ አበባ አስተዳደር የፅዳት እና ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ኤጀንሲ ሲሆን ኤጀንሲው ደግሞ ለፓርኩ ለሠጠው የአገልግሎት ክፍያ ፓርኩ ውስጥ ጥቅም ላይ በዋለ በውሃ ቢል ላይ ደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት ክፍያ እንዲጨመር በማድረግ ነው፡፡
- በሐዋሳ ደግሞ ቆሻሻ ከሚያነሱ ሁለት ማህበራት ጋር ፓርኩ ውል የገባ ሲሆን ማህበራቱ ለሚሰጡት ደረቅ ቆሻሻ የማንሳት አገልግሎት የሐዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ ክፍያ በየወሩ ይፈፅማል፡፡ ፓርኩ ደግሞ ለሠጠው አገልግሎት የኦፐሬሽን ማኔጅመት ክፍያ ለፅዳት፣ ለግሪነሪ እና ለደረቅ ቆሻሻ ማስወገድ በሚል ርዕስ ከባለሀብቶች የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፡፡
- በዚሁ አግባብ የፓርኮች የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድን ሥርዓት በተመለከተ በፓርኩ ውስጥ ሁለት አይነት የፍሳሽ ማጣሪያዎች ያሉ ሲሆን እነሱም Sewer Treatment Plant (STP) and Effluent Treatment Plant (ETP) ይባላሉ፡፡ STP ከሽንት ቤት፣ ከኩሽና፣ ከሻውር እና ከልብስ እጥበት ምክንያት የሚፈጠርን ፍሳሽ የሚያጣራ ሲሆን ETP ደግሞ በምርት ሂደት የተፈጠረን የኢንዱስትሪ ፍሳሽ ለማጣራት ያገለግላል፡፡
- በመሆኑም ፓርኮች ፍሳሽ ቆሻሻን ለማጣራት የተሰሩ የጋራ የፍሳሽ ማጣሪያዎች መሰረተ ልማቶች ያሏቸው ሲሆን የኢንዱስትሪ እና የማዘጋጃ ቤታዊ ፍሳሾች (domestic waste waters) ለየብቻ ይጣራሉ፡፡ አንዳንድ ፓርኮች ደግሞ ከሁለት

አንዱ አይነት የፍሳሽ ማጣሪያ ይኖራቸዋል፡፡ ከማምረቻ ሽዶች የሚለቀቅ የኢንዱስትሪ እና የማዘጋጃቤታዊ ፍሳሽ (domestic waste water) ለብቻ በተሠራላቸው የተለያየ የፍሳሽ መስመር እንዲጓጓዙ ተደርጎ ለየብቻ በማዕከል እንዲጣሩ ይደረጋል፡፡

- ከፍሳሽ አለቃቀቅ ቁጥጥር ጋር በተያያዘ በሀዋሳ ኢ/ፓርክ እያንዳንዱ የኢንዱስትሪ ፍሳሽ የሚለቅ ባለሀብት ከማምረቻ ሽዱ ወደ ዋና የፍሳሽ መስመር ፍሳሹን ከመልቀቁ በፊት የተለያየ መጠን ያላቸው እስክሪኖች (different diameter screens) መትከል ይኖርበታል፡፡ ምክንያቱም ከሚለቀቀው ከፍሳሽ ጋር የጨርቅ ቁርጥራጮች፣ ክር ፣ የውሃ መጠጫ ፕላስቲክ እና የመሳሰሉት ቆሻሻዎች የፍሳሽ መስመሩን ሊደፍኑት ስለሚችሉ ነው፡፡ በዚሁ አግባብ ባለሃብቶች እስኪሪኖች መትከል ብቻ ሳይሆን በየጊዜው ማፅዳት ስላለባቸው ቁጥጥር ይደረጋል፡፡ ሌላው ባለሀብቶች ቢያንስ ለ72 ሠዓት የኢንዱስትሪ ፍሳሽ የሚይዝ ታንከር (holding tank) ይገነባሉ ፣ምክንያቱም ድንገት የፍሳሽ ማጣሪያው ቢበላሽ እስኪጠገን ድረስ ምርት ሳይስተጓጎል ፍሳሻቸውን ለሶስት ቀን መያዝ እንዲችሉ ለማድረግ ነው፡፡
- በተጨማሪ የኢንዱስትሪ ፍሳሽ ከሚለቁ ማምረቻ ሼዶች የፍሳሽ ናሙና በየቀኑ ተወስዶ የላብራቶሪ ፍተሻ ይደረግበታል፡፡

# አባሪ 3፡ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ኮርፖሬሽን ድርጅታዊ መዋቅር

**የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ድርጅታዊ መዋቅር**



## አባሪ 4፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች(Evaluative Criteria)

**ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት:-** <u>የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን</u>

**የኦዲት አካባቢ፡-** <u>የኢንዱስትሪ ፓርኮች የተቀናጀ የደረቅ እና ፈሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት ውጤታማነትን መገምገም</u>

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ<br>(Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት<br>(Evaluative Criteria) |
|---|---|
| 1. የኢንዱስትሪ ፓርኮች በተጠናው የግንባታ ዲዛይንና በውል መሰረት ተጠናቀው **የለማ መሬትና** የመሰረተ ልማት ተሟልቶ፤ ለአልሚ የማስተላለፉ ሂደት ውጤታማ መሆኑን መገምገም | 1. ኮርፖሬሽኑ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ሲገነቡ የአካባቢና የማሕበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ ሊያደርጉና በሚመለከታቸው ስልጣን የተሰጣቸው ተቆጣጣሪ መ/ቤቶች ተገምግሞ ፈቃድ የተሰጣቸው ስለመሆኑ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡(ምንጭ፡- የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁ.299/1995 እና የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ከ2008-2012 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ገፅ 30፤31) |
| | 2. ኮርፖሬሽኑ ከፍሳሽ ማከሚያዎች የሚመነጭን ግግር ዝቃጭ ቆሻሻ (Sludge) አካባቢያዊና ማህበራዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ ለማስወገድ የሚሆን ቦታ (የሳኒተሪ ላንድ ፊል) በዲዛይኑ ውስጥ አካቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡(ምንጭ፡- የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ከ2008-2012 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ገፅ 70) |
| | 3. ኮርፖሬሽኑ የኢንዱስትሪዎች የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ ግንባታ ስራዎች በዲዛይኑ ውስጥ ተካተው፤በተያዘው ዕቅድና ውል መሰረት በወቅቱ ተጠናቀው ወደ ስራ ስለመግባታቸው ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡(ምንጭ፡-የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ከ2008-2012 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ገፅ 70) |
| | 4. ኮርፖሬሽኑ የፍሳሽ ማጣሪያዎች በአግባቡ መጠበቃቸውን |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) |
| --- | --- |
| | ፤መጠገናቸውንና በትክክል አገልግሎት እየሰጡ መሆናቸውን የሚከታተልበት ስርአት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ምንጭ፡-ለኢንዱስትሪ ፓርኮች የወጣ የሚንስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁ. 417/2009 አንቀፅ 13/4/ፊደል ተ.ቁ./ሸ/ |
| | 5. ኮርፖሬሽኑ የለማ ኢንዱስትሪ ፓርክን ለአምራች ድርጅቶች ሊያቀርብ/ሊያስተላልፍ ይገባል፡፡ ምንጭ፡-ለኢንዱስትሪ ፓርኮች የወጣ የሚንስትሮች ም/ቤት አዋጅ ቁ. 886/2007 አንቀፅ 6/ ንዑስ አንቀፅ 6.እና አንቀፅ 8/4. |
| | 6. ኮርፖሬሽኑ የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅቶች የፋብሪካው የዋናው የፍሳሽ ማጠራቀሚያ መስመር ድንገተኛ ብልሽትና ጥገና ሲደረግ ቢያንስ ለ72 ሰአታት የቆሻሻ ውሃ የሚይዝ የቤት ውስጥ እና የኢንዱስትሪ ፍሳሽ ማጠራቀሚያ ታንከር እንዲገነቡ ሊያደርግ ይገባል፡፡ምንጭ፡-የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁ.243/2011. እና standard operation procedure መደበኛ የአሠራር ሂደት ገፅ 25.እና standard operation procedure page 25 |
| 2.ከኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚመነጩ ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻን ለማስተዳደር የተዘረገው የአሰራር ስርዓት ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤ | 7. ኮርፖሬሽኑ በየኢንዱስትሪዎቹ ቆሻሻን ለማስተዳደር የአሰራር ስርአት መዘርጋቱን እንዲሁም ተግባራዊ ስለመደረጉ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡ምንጭ፡-የኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁ.417/2009 አንቀፅ 15/3. |
| | 8. ኮርፖሬሽኑ ከኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚመነጩ ቆሻሻዎችን የመቀነስ፤ እንደገና የመጠቀም፤ መልሶ ለሌላ ምርት ግብዓትነት የማዋል ስልቶች መተግበራቸውን ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምንጭ፡- መልካም ተሞክሮ |
| | 9. ኮርፖሬሽኑ የኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚያመነጩት ቆሻሻ የአደገኛነት ደረጃቸው ተለይቶ በግልፅ ሊታይ በሚችል |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) |
|---|---|
| | መልኩ ስለመቀመጣቸው ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ ምንጭ- አደገኛ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አዋጅ ቁ.1090.አንቀፅ 6/2፡፡ |
| | 10. ኮርፖሬሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም አምራች ድርጅት በጊዜያዊ የማከማቻ ስፍራ አደገኛ ቆሻሻን ከአንድ ወር በላይ እንዳያከማች ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ ምንጭ- አደገኛ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አዋጅ ቁ.1090.አንቀፅ 6/4 |
| | 11. ኮርፖሬሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚመነጨውን ዝቃጭ በተመለከተ የዝቃጭ አያያዝና አወጋገድ ስርአት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ምንጭ፡-Sludge Management Guideline For Bole Lemi and Kilinto Industrial Parks ዝቃጭ አስተዳደር መመሪያ ለቦሌ ለሚ እና ቂሊንጦ ኢንዱስትሪያል ፓርኮችገፅ 27 |
| | 12. ኮርፖሬሽኑ በፓርኮች ውስጥ ያለውን የዝቃጭ አያያዝና አወጋገድ በዕቅድ በመያዝ ኦዲት ሊያደርግና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ ምንጭ፡-Sludge Management Guideline For Bole Lemi and Kilinto Industrial Parks ዝቃጭ አስተዳደር መመሪያ ለቦሌ ለሚ እና ቂሊንጦ ኢንዱስትሪያል ፓርኮችገፅ 27 |
| | 13. ኮርፖሬሽኑ የኬሚካል ፍሳሽ ያላቸው በፓርኩ ውስጥ የሚገኙ ድርጅቶችን በመለየት በእያንዳንዳቸው የፍሳሽ መለኪያ መሳሪያ (flow meter) እንዲገጠም ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምንጭ፡-የማኔጅመንት ቃለ ጉባኤ የካቲት 11/2011ዓ.ም |
| | 14. ኮርፖሬሽኑ የኢንዱስትሪ ፍሳሽ ከሚለቁ ማምረቻ ሼዶች የሚወጣ ፍሳሽን ወደ አካባቢው ከመልቀቁ በፊት በማከም በኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ብክለት ለመቆጣጠር የወጣውን ደረጃ ወይም መመዘኛ (parameter) እንዲሁም በኮርፖሬሽኑ የተዘጋጀውን ደረጃ Blended Parameters ማሟላቱን |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) |
|---|---|
| | ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ ምንጭ፡-በኮርፖሬሽኑ የተዘጋጀውን Blended Parameters እና የኢንዱስትሪ ብክለት ለመቆጣጠር የወጣውን ደረጃ ወይም መመዘኛ (parameter). |
| | 15. ኮርፖሬሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚገኙ አምራቾች የሚለቁትን ፍሳሽ የኬሚካል ሎድ (መጠን) ታሳቢ በማድረግ ሊለካ ይገባል፡፡መልካም ተሞክሮ standard operation procedure (sop) p. 26 |
| | 16. ኮርፖሬሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚገኙ አምራቾች ከሚለቁት ፍሳሽ የሚሰበሰብ ገቢ ተመጣጣኝና የፍሳሽ ቆሻሻን ለማከም የሚያስችል ወጪን ያገናዘበ፤ወቅታዊ ማስተካከያ የሚደረግበት እንዲሆንና ለዚሁ አላማ እንዲውል ሊያደርግ ይገባል፡፡ መልካም ተሞክሮ እና standard operation procedure (sop) p. 26 |
| 3.ኮርፖሬሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች የስራ ቦታና ግቢ የሰራተኞች ደህንነትና ጤንነት ሁኔታን የክትትል ስርአት ውጤታማነት መገምገም ፤ | 17. ኮርፖሬሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚሰሩ ሴት ሰራተኞች ለጤናቸው ጎጂ በሆኑ የስራ መስኮች አለመሰማራታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፤፤ ምንጭ፡- የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀፅ 87 |
| | 18. ኮርፖሬሽኑ በእያንዳንዱ ኢንዱስትሪ ፓርክ የአካባቢ ጥበቃ ባለሙያ በቋሚነት በመመደብ የአካባቢ ሁኔታዎች ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምንጭ፡-መልካም ተሞክሮ sludge management guide line for bole lemi ገጽ17 |
| | 19. ኮርፖሬሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚሰሩ ሰራተኞች የስራ ላይ ደህንነታቸውንና ጤንነታቸውን የጤናና የሙያ ደህንነት ባለሙያ በመመደብ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡ |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) |
|---|---|
| | ምንጭ፡- የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀፅ 92/2 |
| 4.ኮርፖሬሽኑ የአካባቢ ደህንነትን በጠበቀ መልኩ ስራውን እንዲሰራ ከሚያግዙት ባለ ድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበት የአሰራር ስርአት እና የመረጃ አያያዝ ስርዓት ውጤታማ መሆኑን መገምገም፡፡ | 20. ኮርፖሬሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ለሚሰሩ ሰራተኞች የደረቅ እና ፈሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና እንዲያገኙ ሊያደርግ ይገባል፡፡(ምንጭ፡- የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የ2012 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ገፅ 20) |
| | 21. ኮርፖሬሽኑ ኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚጠቀሟቸው ኬሚካሎች መረጃ በየአመቱ ለኢንዱስትሪ ሚ/ር ሪፖርት ሊያደርግ ይገባል፡፡ምንጭ፡-የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ምዝገባ አስተዳደር አዋጅ ቁ.1075/2010 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 3 |
| | 22. ኮርፖሬሽኑ የኢንዱስትሪ ፓርኮች የአካባቢ ደህንነትንና ጥበቃን በተመለከተ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ሊሰራ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡-Integrated Solid Waste Management Guideline for Textile and Garment Based Clusters of Industrial Parks, In IPDC ገፅ 16 |
| | 23.ኮርፖሬሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም አደገኛ ቆሻሻ አመንጪ ድርጅት በአደገኛ ቆሻሻ ጊዜያዊ ማከማቻ ማዕከሉ የሚገኙትን የአደገኛ ቆሻሻ አይነትና መጠን እና ባህሪ የተመለከተ መዝገብ እንዲይዙ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>ምንጭ- አደገኛ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አዋጅ ቁ.1090.አንቀፅ 6/3 |
| | 24. ኮርፖሬሽኑ ኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚጠቀሙበት ለፍሳሽ ማጣሪያ የሚሆን የኬሚካል አቅርቦት እና ዝቃጭ (Sludge) ማኔጅመንት ውጤታማ ለማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) |
|---|---|
| | ጋር በጋራ ሊሰራ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡-የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የ2013 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ገፅ 35) |
| | 25. ኮርፖሬሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ከሚገኙ አምራቾች የሚመነጩ ቆሻሻዎችን እንዲያስወግዱለት የስምምነት ውል የተዋዋላቸው ማህበራት (ቆሻሻ ሰብሳቢዎች) ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ቆሻሻን ለመሰብሰብ፣ ለማጓጓዝ እና ለማስወገድ ህጋዊ ፍቃድ ያላቸው መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ምንጭ፡-Integrated Solid Waste Management Guideline for Textile and Garment Based Clusters of Industrial Parks, In IPDC ገፅ 14 |
| | 26.ኮርፖሬሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች የአረንጓዴና የጋራ ቦታዎች እንክብካቤ ልማት ተግባራዊ መደረጉን ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምንጭ፡-ስለኢንዱስትሪ ፓርኮች አስተዳደር የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁ. 417/2009 አንቀጽ 13 ሰ |

## አባሪ 5፡ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው መጠይቅ የቀረበላቸው እና የመስክ ጉብኝት የተደረገባቸው ኢንዱስትሪ ፓርኮችና የሚመለከታቸው አካላት ዝርዝር

1. አዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ
   - ጆተን የቀለም ፋብሪካ
   - አንቴክስ ቴክስታይል ኃ/የተ/የግ/ማ
   - ኪንግደም (መረጃ ለመስጠትና ፋብሪካውን ለማስጎብኘት ፈቃደኛ ያልሆነ)
   - የአዳማ የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ባለስልጣን ጽ/ቤት
   - በአዳማ ኢ/ፓርክ ዙሪያ ላሉ ነዋሪዎች
2. ድሬዳዋ ኢንዱስትሪ ፓርክ
   - ሀም ፕላስት የሲሚንቶ ከረጢት ማምረቻ
   - ውሺ ነምበር ዋን ኮተን ኢትዮጵያ ቴክስታይል
   - አንድሪያ ጫማ ፋብሪካ
   - የድሬደዋ አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት
3. ቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ
   - ጂይ ጂይ ቴክስታይልስ ኃ/የተ/የግ/ማ
   - ልዩ ሸታእ ፋብሪካ
   - አሸተን አፓረል ማኑፋክቸሪንግ
   - ሱፍሌት ብቅል ፋብሪካ
   - ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
   - ለቦሌ ለሚ ኢ/ፓርክ የአካባቢና ማህበራዊ ጥበቃ ባለሙያ
   - በቦሌ ለሚ ኢ/ፓርክ ዙሪያ ላሉ ነዋሪዎች
4. ሐዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ
   - ጄፒ ጋርመንት ኢትዮጵያ ኃ/የተ/የግ/ማ

- ጂፒ ቴክስታይል ኢትዮጵያ ኃ/የተ/የግ/ማ
- ናሳ ጋርመንት ኃ/የተ/የግ/ማ
- ኢንዶቼይን አፓረል ኃ/የተ/የግ/ማ (**መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነ**)
- ለሐዋሳ ኢ/ፓርክ የአካባቢና ማህበራዊ ጥበቃ ባለሙያ
- በሲዳማ ብ/ክ/መ/ለሃዋሳ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ቁጥጥር ጽ/ቤት
- በሐዋሳ ኢ/ፓርክ ዙሪያ ላሉ ነዋሪዎች
- በሐዋሳ ሃይቅ ዙሪያ ለሚገኙ ሁለት አሳ አስጋሪዎች ማህበር

5. የኢትዮጵያ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን

## አባሪ 6፡ በኦዲቱ ወቅት የተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች ዝርዝር፡-

1. የኮርፖሬትን የመቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 326/2007 ፣
2. የኢንዱስትሪ ፓርኮች አዋጅ ቁጥር 886/2007 ዓ.ም፣
3. የኢንዱስትሪ ፓርኮች ደንብ ቁጥር 417/2009
4. የአደገኛ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አዋጅ ቁ.1090/2010 ፣
5. የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ ቁ.513/1999 ፣
6. የኢንዱስትሪ ብክለት መከላከያ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁ.159/2001፣
7. የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁ.299/1995
8. የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የአምስት አመት ስትራቴጂክ ዕቅድ (2013-2017) አንደኛ ረቂቅ
9. የስራ አመራር እና የቦርድ ቃለ ጉባኤዎች፣
10. የየዓመቱ ዕቅድ እና ዕቅድ አፈፃፀሞችን (ከ2011-20015 ዓ/ም) ፣
11. Standard operation procedure for Industrial Park
12. የተለያዩ ጥናቶች እና መመሪያዎች፣